# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## *በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የወጪ ንግድ አፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን ለመገምገም የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት*



*መጋቢት 2007 ዓ.ም*

*አዲስ አበባ*

# ማውጫ

ማውጫ ........................................................................................................................ i

ክፍል አንድ ........................................................................................................................ 1

መግቢያ ........................................................................................................................ 1

የኤጀንሲው  ዓላማ፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ሥልጣንና ተግባር; ........................................................................ 1

ሥልጣንና ተግባር ........................................................................................................................ 2

የኤጀንሲው አደረጃጀትና የሰው ኃይል ........................................................................................... 3

የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ ........................................................................................................ 4

የኦዲቱ ዓላማ ........................................................................................................................ 4

የኦዲቱ አካባቢ ........................................................................................................................ 5

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫና መስፈርት .............................................................................................. 5

የክዋኔ ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ............................................................................................................ 6

የሥራ ሂደት መግለጫ (Process descriptions) ................................................................................ 8

ክፍል ሁለት ........................................................................................................................ 9

ግኝቶች ........................................................................................................................ 9

ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በተመለከተ የኢንቨስትመንት ድጋፍ አሰጣጥ፣ የማበረታቻ ስርዓትና በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የተዘረጋው አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤ ........................................ 9

የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ ለማቆየትና ለማበረታታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓትን በተመለከተ፤ ........................ 9

ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሆኑ መሬቶችን በማጥናት ለባለሀብቶች ማስተዋወቅን በተመለከተ፤ ........................................ 11

በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ወደልማት ከመግባታቸው በፊት የአዋጭነት ጥናት ማቅረባቸውን በተመለከተ፤.13

ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ለባለሀብቶች በወቅቱ እንዲሟላላቸው የተዘረጋ ስርዓትን በተመለከተ፤ ........................................ 14

አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስ...ወዘተ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤ ........................................ 18

የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች  በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ ማድረጉን በተመለከተ፤ ........................................ 19

የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉና ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በአግባቡና በወቅቱ ለታቀደላቸው አላማ መዋላቸውን በተመለከተ፤ ........................................ 20

ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምርት እና ምርታማነትን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ስርዓት ዘርግቶ በአገር ውስጥ እና በዓለም ዓቀፍ ገበያ ጥራቱን የጠበቀ ተወዳዳሪ ምርት ለማምረት እንዲቻል የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 22

የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በአትክልትና ፍራፍሬ በኮንትራት ልማት የሚሳተፉ አርሶ አደሮችን (አውቶግሮዎሮችን) በመመልመል የስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፤........ 22

የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን ውጤታማ የሚያደርጉ የምርት አመራረትና አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን በመሰብሰብና ማንዋሎች በማዘጋጀት በስልጠና እና ሰርቶ ማሳያ ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፤ ........ 23

ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች አለም አቀፍ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችንና ስታንዳርዶችን ያሟሉ መሆናቸውን በተመለከተ፤ ........ 25

የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የምርት ግብዓት በወቅቱና በሚፈለገው መጠን እንዲቀርብ ድጋፍና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ 26

በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች ዕቅድ እና አፈፃፀም ክትትል የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 27

ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ጥራቱን የጠበቀ እና ተወዳዳሪ ምርት ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንዲቻል ድጋፍና ክትትል ማድረጋቸውን እንዲሁም ከአልሚ ባለሀብቶች፣ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 28

የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላኪ ድርጅቶችና ዩኒየኖች የውጪ ንግድ አፈፃፀም መከታተሉን በተመለከተ፤.28

የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎች ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ 30

የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዣ፣ የትራንስፓርትና ሌሎችም የሎጂስቲክስ ፍላጎቶችን እንዲሟሉላቸው ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ 31

የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ተጠቃሚ መሆናቸውን በተመለከተ፤ ........ 32

የሀገሪቱን የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 33

ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ዘርፉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፤ ........ 34

የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤትን በተመለከተ፤ ........ 35

የስትራቴጂክ እና ዓመታዊ ዕቅድ እና የዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ፤ ........ 35

ክፍል ሦስት ........ 38

መደምደሚያዎች ........ 38

ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በተመለከተ የኢንቨስትመንት ድጋፍ አሰጣጥ፣ የማበረታቻ ስርዓትና በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የተዘረጋው አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 38

ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምርት እና ምርታማነትን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ስርዓት ዘርግቶ በአገር ውስጥ እና በዓለም ዓቀፍ ገበያ ጥራቱን የጠበቀ ተወዳዳሪ ምርት ለማምረት እንዲቻል የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 39

የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ጥራቱን የጠበቀ እና ተወዳዳሪ ምርት ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንዲቻል ድጋፍና ክትትል ማድረጋቸውን እንዲሁም ከአልሚ ባለሀብቶች፣ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ....................40

ክፍል አራት....................42

የማሻሻያ ሀሳቦች....................42

አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) ....................47

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ:- የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የውጪ ንግድ አፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን መገምገም፤ ....................47

አባሪ 2 ፡የኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት የስራ ፍሰት ....................53

አባሪ 3፡ የልማትና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት የስራ ፍሰት ....................54

አባሪ 4፡ የገበያ ማስፋፊያ ጥናትና ጥራት ክትትል ዳይሬክቶሬት የስራ ፍሰት....................55

አባሪ 5፡ በናሙና የተመረጡ ክልሎችና ካምፓኒዎች በአካል በመሄድ መረጃ የተሰበሰበባቸው ....................56

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

1. የሆርቲካልቸር ዘርፍ የሚከታተለውና የሚደግፈው አካል ያልነበረውና ነገር ግን በንግድ ሚኒስቴር ስር የኤክስፖርት አፈፃፀም መረጃ የሚመዘገብና ሪፖርት የሚደረግበት አሰራር ብቻ የነበረ ሲሆን ከ2001 የበጀት አመት ጀምሮ የሆርቲካልቸር የልማት (የአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ቕርብስ) ዘርፍ ውጤታማነት ወደተሻለ የእድገት ደረጃ ለማሸገገር እንዲቻል በተሻሻሉ የቴክኖሎጂ ፓኬጆች የታገዘና በግብይት ሰንሰለት ውስጥ የተቀመጡት መስፈርቶችና የተጠቃሚውን ፍላጐት ያሟሉና በአለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶች በብዛትና በጥራት ማቅረብ የሚችል የተዋጣለት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለማድረግ የተጠናከረ የፖሊሲ፣ የሙያና የአስተዳደራዊ ድጋፍ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፤ ይህንን ሀላፊነት በባለቤትነት እንዲያስተባብርና እንዲመራ የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው በደንብ ቁጥር 152/2008 ተቋቁሟል፡፡ የሖርቲካልቸር ኢንድስትሪ ልማት በውስን መሬት ላይ ከፍተኛ የሰው ጉልበትና ካፒታል በመጠቀም በሀገራችን የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ሂደት ውስጥ ከፍተኛ የስራ ዕድልና የውጪ ምንዛሬ ገቢ እንዲሁም ለአግሮ ኢንዱስትሪ ልማት መሰረታዊ ጥሬ ዕቃዎች በማቅረብ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ሲሆን፣ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ሁለተኛው ምዕራፍ ማገባደጃ (2007 በጀት ዓመት) ላይ ከዘርፉ 1.48 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ለማስገባት ግብ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ ውስጥ የአትክልትና ፍራፍሬ ንዑስ የልማት ዘርፍ 64 በመቶ የገቢ ድርሻ የያዘ ሲሆን፣ የአበባ ንዑስ የልማት ዘርፍ ደግሞ ቀሪውን 36 በመቶ ይሸፈናል፡፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን አምስተኛ ዓመት ላይ የሖርቲካልቸር ኢንዱስትሪ ግብ ከአጠቃላይ ሀገራዊ የወጪ ንግድ ገቢ ግብ አንፃር ሲታይ ከ7 እስከ 8 በመቶ ድርሻ እንደሚያሟላ ግብ ተቀምጧል፡፡

## የኤጀንሲው ዓላማ፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ሥልጣንና ተግባር;

### ዓላማ

2. የኤጀንሲው ዓላማዎች፡-
   - የሖርቲካልቸር ምርትና ምርታማነት በተፋጠነና በቀጣይነት እንዲያድግ የማብቃት፤
   - ዓለም አቀፍ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ የሖርቲካልቸር ምርቶች ለውጪ ገበያ በዓይነትና በብዛት የሚያቀርብበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤ እና
   - ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችን ያስተባብራል፡፡

## ***ራዕይ***

3. *ሀገራችን ኢትዮጵያ በኤክስፖርት መር የሆርቲካልቸር ኢንዱስትሪ ልማት ከአፍሪካ ሀገራት ቀዳሚ ሆና ማየት የሚል ነው፡፡*

## ***ተልዕኮ***

4. *ባለድርሻ አካላትን አቀናጅቶ በማስተባበር የተሻለ የእርሻ አሰራር መስፈርቶች እና ስታንዳርዶች ማለትም፤ የአከባቢ ጥበቃ፣ ማህበራዊ ግዴታና ደህንነት መሰረት ያደረገ የኮሜርሻል እና የኮንትራት አርሶ አደሮች(የአውት ግሮወሮች) ልማት እንዲስፋፋና ውጤት እንዲያስመዘግብ ተከታታይነት ያለው የአቅም ግንባታ፣ የግብይት ማስፋፋትና የኢንቨስትመንትና ፕሮሞሽን ድጋፍ ስራዎች በማጠናከር እንዱስትሪው ለሀገሪቱ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ድርሻ ላይ አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ማብቃት፤*

## *ሥልጣንና ተግባር*

5. *ኤጀንሲው በደንብ ቁጥር* 152/2008 *መሰረት የተለያዩ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡እነዚህም፡-*
   - *የሖርቲካልቸርን ዘርፍ ፈጣን እድገትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያግዝ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ (የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር) ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤*
   - *በሖርቲካልቸር ልማት ለሚሰማሩት ባለሀብቶች ለአዋጭነት ጥናት መረጃ ይሰጣል፣ ከክልል አካላት ጋር በመተባበር መሬትና የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤*
   - *የመሰረተ ልማት በወቅቱ እንዲያገኙ ለግንባታው ከውጪ አገር የሚገዙ ግብዓቶች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ከአገር ውስጥ የሚገዙትን የግንባታ እቃዎች በወቅቱ እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤የግንባታውን አፈፃፀም ይከታተላል፤*
   - *የግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት የሚሻሻልበትን ሁኔታ በማጥናት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤*
   - *በሖርቲካልቸር ልማት ከአርሶአደሩ ጋር ተዋውለው ለመሰማራት የሚፈልጉትን ባለ ሀብቶች ከክልሎችና ከአርሶ አደር ማህበራት ጋር በመተባበር በአርሶ አደር ምልመላና አደረጃጀት ያግዛል ስለዩሮ-ጋፕ(የአውሮፓ ሕብረት የግብርና ሰብሎች አመራረትና*

እንክብካቤ የጥራት መስፈርት) ሥልጠና ይሰጣል፣ የአሰራር ማንዋል ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

- ከክልል የሰራተኛ ጉዳይ ፅ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሰው ኃይል አቅርቦት እንዲመቻች ያደርጋል፤
- የሖርቲካልቸር ኤክስፖርት ምርቶች በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪነታቸውን ለማረጋገጥ ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ በመነሳት ስለተሻለ አመራረት፣ ምርት እንክብካቤ፣ ጥራትና የምግብ ደህንነት ከሖርቲካልቸር ማህበር ጋር በመተባበር ሥልጠናና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣ የመስፈርቶችና የኤክስቴንሽን ፓኬጆችና ማንዋሎች እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤
- ጥራቱን የጠበቀ የንግድ የመሰረተ ልማት ግንባታ፣ ድግፍ ሰጪ ተቋሞችና አገልግሎቶች እንዲስፋፋ ከሚመለከታቸው ጋር ይተባበራል፤
- ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሎጂስቲክስ ፍላጎት ጥናት በማካሄድ የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቅድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- የሖርቲካልቸር ዘር አልሚዎች ወደ ኢትዮጵያ በስፋት የሚገቡበትን ሁኔታ በማጥናት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቅድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- የሖርቲካልቸር ገበያ ጥናት ያካሂዳል፣ የገበያ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያሰራጫል፣ የሖርቲ ካልቸር አምራችና ላኪዎች በዓለም አቀፍ ንግድ ትርዒቶች ላይ እንዲሳተፉ ሁኔታዎች ያመቻቻል፤
- የሆርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለድርሻዎች የሚሳተፉበት ቋሚ መድረክ በማቋቋም በጋራ ለልማቱ የሚያግዙ እርምጃዎችን ይወስዳል፤ የሆርቲካልቸር ልማት ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ የሚሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## የኤጀንሲው አደረጃጀትና የሰው ኃይል

6. ኤጀንሲው የሚመራው በተቋሙ የበላይ አመራር አካል በሆኑ በዋና ዳይሬክተር ሲሆን ተጠሪነቱም ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ነው፡፡ አምስት(5) ዳይሬክተሮች፣ ሶስት መምሪያዎች እና አንድ(1) ጽ/ቤት ይገኛሉ ስዕላዊ መግለጫ በአባሪ 1 ይመልከቱ፡፡ ለኤጀንሲው በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል 178 ሲሆን እስከ ታህሳስ 2007 ዓ.ም ያለው የሰው ኃይል 77 ነው፡፡ ከላይ በመ/ቤቱ በቋሚነት ከተጠቀሱት ጠቅላላ ሰራተኞች ዋና ዳይሬክተሩን ይጨምራል፡፡

## የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ

| በጀት ዓመት | የበጀት ዓይነት | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | % |
|---|---|---|---|---|
| 2003 | መደበኛ በጀት | 6,636,629.14 | 4,574,623.68 | 68.9 |
| | የካፒታል በጀት (HPTC) | 5,748,078.00 | 1,625,662.46 | 28.3 |
| | **ድምር** | **12,384,707.14** | **6,200,286.14** | **50.1** |
| 2004 | መደበኛ በጀት | 8,758,560.00 | 4,461,583.03 | 50.9 |
| | የካፒታል በጀት (HPTC) | 3,151,500.00 | 472,192.65 | 15.0 |
| | **ድምር** | **11,910,060.00** | **4,933,775.68** | **41.4** |
| 2005 | መደበኛ በጀት | 9,521,640.00 | 7,289,668.26 | 76.6 |
| | የካፒታል በጀት (HPTC) | 1,053,950.00 | 807,433.81 | 76.6 |
| | **ድምር** | **10,575,590.00** | **8,097,102.07** | **76.6** |
| 2006 | መደበኛ በጀት | 17,083,271.00 | 10,619,138.34 | 62.2 |

## የኦዲቱ ዓላማ

7. የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና እና ጥራቱን የጠበቀ ምርት ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ኤጀንሲው የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩና በዘርፉ የወጡትን ህግና ደንቦች መሰረት ያደረገ እንዲሁም በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግብን ለመምታት የሚያስችልና ከፍተኛ የስራ ዕድልና የውጭ ምንዛሬ ገቢ ለማስገኘት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የተከሰቱ የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የተቋቋመበትን ዓላማ እንዲያሳካ የሚያግዝ ድጋፍ ለማድረግና በኤጀንሲው አሰራርም ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲቱ አካባቢ

8. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Potential audit Area) በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የወጪ ንግድ አፈፃፀም ብቁና ውጤታማ በሆነ መንገድ እየተከናወነ መሆኑን እና ለዚሁ ተግባር የዋለው ግብዓት ያስገኘውን ተመጣጣኝ ውጤት (Value for Money) ለማረጋገጥ የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫና መስፈርት

### <u>የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች</u>

9. በተመረጠው የኦዲት አካባቢ መሰረት በማድረግ ሶስት ዋና ዋና እና አራት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፦
   1. ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የኢንቨስትመንት ድጋፍ አሰጣጥ፣ የማበረታቻ ስርዓትና በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የተዘረጋው አሰራር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
      - 1.1 የኢንቨስትመንት ድጋፍ አገልግሎት ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል የአሰራር ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤
      - 1.2 በመንግስት የወጡ ልዩ ልዩ የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች በአግባቡ ስራ ላይ የሚውልበትና ኢንቨስትመንቱን ከመደገፍ አንፃር የሚከሰቱ ችግሮችን በወቅቱ በመለየት አፋጣኝ መፍትሔ ለመስጠት ኤጀንሲው ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤
   2. ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምርት እና ምርታማነትን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ስርዓት ዘርግቶ በአገር ውስጥ እና በዓለም ዓቀፍ ገበያ ጥራቱን የጠበቀ ተወዳዳሪ ምርት ለማምረት እንዲችሉ የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
   3. ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ጥራቱን የጠበቀ እና ተወዳዳሪ ምርት ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል ማድረጋቸውን እንዲሁም ከአልሚ ባለሀብቶች፣ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ፤

3.1 በዘርፉ የተሰማሩ ባለሃብቶች ጥራቱን የጠበቀ እና ተወዳዳሪ ምርቶችን ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ የገበያ ጥናት በማካሄድ ትስስር መፍጠሩን፣የውጭ ንግድ የምርቶች ሽያጭ የመንግስት ፖሊስን ተከትሎ መፈፀሙን መገምገም፤

3.2 በዘርፉ የተሰማሩ ባለሃብቶች ጥራቱን የጠበቀ ምርት ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ባለሃብቶች እንዲያቀርቡ ኤጀንሲው ከአልሚ ባለሀብቶች፣ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ፤

የሚሉት ናቸው፡፡

## <u>የኦዲት መመዘኛ መስፈርት</u>

10. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሶስት የኦዲት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 43 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) የተዘጋጁ ሲሆን፣ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የኢትዮጵያ የሖርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 152/2008፣ ከ2003-2006 እቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን፣ ከ2003-2007ዓ.ም የስትራቴጅክ ዕቅድ፣ ቃለ ጉባኤ (2003 -2006 ዓ.ም)፣ ሖርቲካልቸር ዘርፍ ስራ አፈፃፀም የሱፐርቪዥን ሪፖርት(በጠቅላይ ሚ/ር ፅ/ቤትና ግብርና ሚ/ር የሱፐርቪዥን ቡድን፣ የሖርቲካልቸር ኢንዱስትሪ ግምገማና የመፍትሔ አቅጣቻዎች ሰነድ ሲሆኑ በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ኤጀንሲ የበላይ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

# የክዋኔ ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

## <u>የኦዲቱ ወሰን</u>

11. የክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2003 እስከ 2006 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የወጪ ንግድ አፈፃፀም በሚመለከት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በፌዴራል ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ፣ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ከክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ እንዲሁም በናሙና

ከተመረጡ የአትክልትና ፍራፍሬ ማምረት ፈቃድ የተሰጣቸውን ኩባንያዎችና የአውትግሮዎር(የኮንትራት አርሶ አደሮች) ማህበራት ያካተተ ነው፡፡

**<u>የኦዲቱ ዘዴ</u>**

12. ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኤጀንሲው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ የተለያዩ ዶክመንቶችን በመከለስና በመተንተን ሲሆን በተጨማሪም ኦዲቱ በናሙና በተመረጡ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ እንዲሁም በናሙና ከተመረጡ 14 አትክልትና ፍራፍሬ ማምረት ፈቃድ የተሰጣቸውን ኩባንያዎችና ሁለት የአውትግሮዎር (የኮንትራት አርሶ አደሮች) ማህበራት ኃላፊዎችን ቃለ መጠይቅ በማቅረብ፣ የመስክ ጉብኝት በማድረግ ማስረጃዎችን በመከለስና በተሰበሰቡት ማስረጃዎች ላይም አስፈላጊውን ትንተናና ንፅፅር (Analysis) በማካሄድ ኦዲቱ ተከናውኗል።

13. የኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክቱሬቱ የኢንቨስትመንት ድጋፍ ተግባራትን ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣ የኢንቨስትመንት ድጋፍ ተግባራት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆኑ መንገዶች እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ ደንበኞች የተሟላ አገልግሎት ማግኘታቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ከስራ ጋር የተያያዙ መንግስት ያወጣቸው አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች በአግባቡ እንዲተረጎሙ ያደርጋል፣ ለደንበኞች ቅሬታ መፍትሄ ይሰጣል ስዕላዊ መግለጫ በአባሪ 3 ይመልከቱ፡፡
14. የልማትና የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት በሆርቲካልቸር ልማት መስክ ያለውን ዓለም አቀፋዊ ክስተቶችን በመዳሰስ ለልማቱ መስፋፋትና መጎልበት የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል በእነዚህ የጥናት ግኝቶች ላይ በመመስረት የባለሀብቶች የማስፋፋት ስራ እንዲጠናከር ያግዛል፤ የመስኩን የልማት አቅጣጫ በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት ፕሮግራሞችን፣ ፕሮጀክቶችንና ዝርዝር ጥናቶችን ያካሂዳል፤ ከዚሁ ጎን ለጎን በልማቱ አፈፃፀም ላይ አጠቃላይ ቅኝት በማድረግ መረጃዎች በመተንተን፣ በጥናቱ ግኝት በመመስረት የሴክተሩ የሀገራዊ የፖሊሲ ሀሳቦችን በማመንጨት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፤ የሆርቲካልቸር ምርታማነትና ጥራትን የሚያጎለብቱ ቴክኖሎጂ ፓኬጆችን በምረጥ፣ በመለየትና በማዘጋጀት በመስኩ የተሰማሩ ባለሀብቶችና አርሶ አደሮች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታዎች በማጥናት ተግባራዊ ያደርጋል ስዕላዊ መግለጫ **በአባሪ 4 ይመልከቱ፡፡**
15. የገበያ ማስፋፊያ ጥናትና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት በሆርቲካልቸር ልማት ተያያዥነት ያላቸው የገበያ፣ የፖሊሲ ነክ ጉዳዮችና ሌሎች መረጃዎች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በማደራጀት ለባለሀብቶችና ለሌሎች አምራቾች ማሰራጨትና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ድጋፎችን የመስጠት ተግባር ያከናውናል፡፡ በዚህ ተግባር ስር በተለይ በኤጀንሲው በቀጥታ ሊሰጡ የማይችሉ ሌሎች የሎጂስቲክስና መሰል የድጋፍ ሥራዎች በሚፈለገው ደረጃ እንዲፈፀሙ ኤጀንሲው ትኩረት ሰጥቶ ተገቢውን የማመቻቸትና የክትትል ስራዎች ያከናውናል ስዕላዊ መግለጫ **በአባሪ 5 ይመልከቱ፡፡**

## ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በተመለከተ የኢንቨስትመንት ድጋፍ አሰጣጥ፣ የማበረታቻ ስርዓትና በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የተዘረጋው አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

### የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ ለማቆየትና ለማበረታታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓትን በተመለከተ፤

16. የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ ከሚመለከታቸው ከክልልና ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ ለማቆየትና ለማበረታታት የሚያስችል የኢንቨስትመንት የማትጊያ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ እና ስለሚሰጠው ድጋፍ ለባለሃብቶች ሊያስተዋውቅ ይገባል፡፡

17. በዚሁ መሰረት እንደሌሎች የመንግስት የወጪ ንግድ የትኩረት አቅጣጫዎች በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የተለያዩ የድጋፍ አይነቶች በጉምሩክ፣ በታክስ እፎይታና በብድር አቅርቦት በመሳሰሉት ተለይተዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በዘርፉ የተሰማሩ ለተወሰኑ ባለለሀብቶች አሁን ባለው የአየር ትራንስፖርት አቅርቦትና የትራንስፖርት ወጪ መናር አንፃር በዘርፉ ተወዳድረው ውጤታማ ሊሆኑ እንደማይችሉ በመገምገም የትራንስፖርት ወጪ ጊዜያዊ ድጎማ የሚያገኙበትን እንዲሁም ከኢትዮጲያ ልማት ባንክ የብድር አቅርቦት የሚገኙበትን የድጋፍ አሰራር ማመቻቸቱን በኦዲት ወቅት ከኤጀንሲውየስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

18. ይሁን እንጂ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ኢትዮጲያ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ያላትን አቅምና ተወዳዳሪነት(Comparative advantage) ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እና በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ በክፍለ አህጉር ደረጃ በተለይም በመካከለኛውና ምስራቅ አፍሪካ ውጤታማ የሆኑ አገሮችን ተሞክሮ በመቀመር በዘርፉ ሊሰማሩ የሚችሉ ባለሀብቶችን በተሻለ ለመሳብ የሚያስችል የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ያገናዘበ፣ ሁሉን አቀፍ፣ ዘላቂነት ያለው እና አስተማማኝ የድጋፍ ማዕቀፍ(Comprehansive incentive package) ያላዘጋጀና በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ ባለሀብቶችም እንዲያውቁት ያልተደረገ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

19. በኤጀንሲው ሊዘጋጅ የሚገባው ሁሉን አቀፍ የድጋፍ ማዕቀፍ የአትክልትና ፍራፍሬን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ዋና ዋና የድጋፍ አይነቶችን ማለትም በግብዓት አቅርቦት ድጋፍ፣ ከምርምርና መሰል ተቋማት በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ በተለይ በዘር ፍተሻ ማለማመድና ማባዛትን በተመለከተ፣ በመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ድጋፍን በተመለከተ፣

በብድር አቅርቦት፣ በውጭ ምንዛሪ አቅርቦትና ዝውውር ድጋፍን በተመለከተ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ በተመለከተ፣ የአለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ለማሟላት የሚያግዝ የቴክኒክና የስልጠና ድጋፍን እንዲሁም ለዘርፉ የሚያስፈልጉ መረጃዎች አቅርቦት እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በመጓጓዝ ሂደት ለሚያጋጥማቸው አደጋና ብልሽት ሊኖር ስለሚችል የዋስትና አቅርቦት ድጋፍ የመሳሰሉ የድጋፍ ዓይነቶችን በዝርዝር በመለየት ድጋፍ የሚሰጠውን አካል ኃላፊነት፣ ድጋፉ ሊገኝ የሚችልበትን ጊዜ፣ በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር በመለየት ከአንድ መስኮት አገልግሎት(One window shopping) መሰረተ ሀሳብን የሚያመላክት ሁሉን አቀፍ የማበረታቻ የድጋፍ ማዕቀፍ ኤጀንሲው ያላዘጋጀና በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶች እንዲውቁት እንዳላደረገ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

20. ከዚህ በተጨማሪ መንግስት በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ያስቀመጠው የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ በጉምሩክ አሰራር ቀልጣፋ ባለመሆን በጉምሩክ ወደብ ላይ ረጅም ጊዜ የሚቆዩ በመሆኑ ባለሀብቶችን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረጋቸው እንደሚገኝ በኦዲት ወቅት ለባለሀብቶች ከቀረበ ቃለመጠይቆችና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

21. በተጨማሪም በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ከ2003-2007ዓ.ም በስትራቴጂክ ዕቅድ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ 23,040.4 ሄክታር መሬት በባለሀብቶች ይለማል ተብሎ ዕቅድ ቢያዝም እስከ 2006 ዓ.ም መጨረሻ በባለሀብቶች የተያዘው መሬት 13,084.2 ሄክታር 57 በመቶ ብቻ መሆኑ ከዕቅድና

| በጀት ዓመት | ለአትክልትና ፍራፍሬ ባለሀብቶች ይተላለፋል ተብሎ የታቀደ መሬት በሄክታር እና አፈፃፀሙ | | |
|---|---|---|---|
| | በስትራቴጂክ ዕቅድ | ዓመታዊ ዕቅድ | ክንውን |
| 2003 | 5,164.7 | 7,198 | 6,156 |
| 2004 | 10,513.4 | 13,483.2 | 12,554 |
| 2005 | 16,080.8 | 19,661.2 | 12,797 |
| 2006 | 23,040.4 | 22,885.4 | 13,084.2 |

ከአፈፃፀም ሪፖርቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

22. የዕቅድ አፈፃፀሙ በከፍተኛ ደረጃ ለምን ሊለያይ እንደቻለ የኦዲት ቡድኑ ለኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በአትክልትና ፍራፍሬ ይለማል ተብሎ በዕቅድ የተያዘው መሬት በጥናት ላይ ተመስርቶ ለዘርፉ በትክክል ሊለማ የሚችለው መሬት ሳይሆን ያለዝርዝር ጥናት አካባቢዎች ብቻ የተለዩ ስለነበር እና በጥናት ላይ ተመስርቶ ባልተዘጋጀ መሬት ላይ የማስተዋወቅ ስራ በመሰራቱ ባለሀብቶች ከመጡ በኃላ በዕቅድ የተያዙት ቦታዎች ባብዛኛው ሊለሙ የማይችሉ በመሆናቸው በዕቅድ የተያዘውና የለማው መሬት ሊለያይ መቻሉን

አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም ኤጀንሲው አሁን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በትክክል ሊለማ የሚችለው የመሬት መጠን ለማጥናት እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

23. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በኤጀንሲው በሆርቲካልቸር ኢንዱስትሪ ልማት ውጤታማ ባለሀብቶች ለመመልመል ቢ.ጋር (ToR) ተዘጋጅቶ ለውጪ ጉዳይ የላኩ መሆናቸውንና በዚህም መሰረት ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የማስተዋወቁን ስራ እየሰራ የሚገኝ መሆኑን፣ ኤጀንሲው በተጠናከረ እና በተደራጀ መልኩ የማስተዋወቁን ስራ እንዳይሰራ የበጀት እና የባለሙያ ችግር ያለበት መሆኑ፣ እንዲሁም ባለሀብቶች በተለያየ አጋጣሚ እርስ በርስ መረጃ በመለዋወጥ ወደ ኤጀንሲው ሲመጡ የማስተናገድና መረጃ የመስጠት ስራ እንደሚሰሩ የገለፁና አትክልትና ፍራፍሬ በተፈጥሮው ቶሎ የሚበላሽ (perishable) እንደመሆኑ ሁሉም አካላት በልዩ እንደሚመለከቱትና ችግሮች ሲከሰቱ ኤጀንሲው የድጋፍ ደብዳቤ ከመፃፍ በዘለለ ችግሮቹ እንዲፈቱ በየጊዜው ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

24. ስለጉዳዩ በነባራዊ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ባለሀብቶችን የመሳብ ሥራ የሚከናወነው በኤጀንሲው ብቻ ሳይሆን ከባለድርሻ አካላትና ከውጭ ሚሲዮኖቻችን ጋር በቅንጅት የሚሰራ ሲሆን በማናቸውም መንገድ ተስበው የሚመጡ ባለሀብቶች ሀገሪቱ ለሆርቲካልቸር ልማት ተስማሚ ስነምህዳር፣ ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ወዘተ… እንዳላት በቂ ግንዛቤ አግኝተው ወደ ልማቱ እንዲገቡ በኤጀንሲው በኩል የሚደረገው ጥረት መኖሩን ለምሳሌ ቆጋቬጅ - ባህርዳር፣ አለምዬ እንጆሪ አምራች - ሆለታ፣ እንዲሁም አሁን ባለው የአየር አገልግሎት ከፍተኛ ክብደት ያላቸውን የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች አጓጉዞ ተወዳዳሪ መሆን ባለመቻሉ በኤክስፖርት ዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች የተገደቡ መሆናቸው፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቀላል ክብደት ባላቸው የዕፀ-ጣእም (herbs) እና በእንጆሪ (Strawberry) ምርት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ተበረታተው ከፍተኛ የማስፋፊያ ጥያቄ እያቀረቡ መሆኑና ይህ ሂደት የወደፊቱ የዘርፉ እድገትን አመላካች መሆኑ ገልፀዋል፡፡

25. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ ለማቆየትና ለማበረታታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የማስተዋወቁን ስራ በስፋት ተግባራዊ በማድረግ ውጤታማ ባለሀብቶችን ባለመሳቡ፣ ማበረታቻዎች በትግበራ ላይ ውጤታማ አለመሆናቸው እና እያደረገ ያለው ድጋፍ ያልተጠናከረ መሆኑ፣ በዘርፉ ባለሀብቶች በስፋት እንዳይገቡና እንዳይበረታቱ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሆኑ መሬቶችን በማጥናት ለባለሀብቶች ማስተዋወቅን በተመለከተ፤

26. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ኢንቨስትመንት አመቺ የሆኑ መሬቶችን በዝርዝር ሊያጠና እና ባለሃብቶችን ለመሳብ የማስተዋወቅ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

27. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ክልሎች ውስጥ በኦሮሚያ(7293.7ሄ/ር)፣ በአማራ(2662ሄ/ር)፣ በደቡብ ክልል በሀዋሳ አርባ ምንጭ ኮሪዶር(1968ሄ/ር)፣በደቡብ ትግራይ (ራያና ቆቦ)(1000ሄ/ር) ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተለዩ ቢሆንም ከኦሮሚያ ክልል ውጭ ያሉት የተለዩ መሬቶች በትክክል ለዘርፉ የሚውሉ ስለመሆናቸው በሆርቲካልቸር ኤጀንሲ ጥናት ያልተከናወነ እና መሰረታዊ መረጃዎች ተለይተው ያልተያዙ መሆኑ ታውቋል፡፡

28. በተጨማሪም በሀዋሳና አርባ ምርጭ ኮሪደር ላይ በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲና በክልሉ በጋራ የተለየውን 1968 ሄ/ር መሬት ወደ መሬት ቋት ለማስገባት በኤጀንሲው ለደ/ብ/ብ /ህ/ክ የመሬት ማስተላለፍና መግባቢያ ሰነድ ረቂቅ የተዘጋጀ ቢሆንም ያልፀደቀ በመሆኑ ለዘርፉ ልማት ሊውል ያልቻለ መሆኑ፣ እንዲሁም በድሬድዋ፣ በጅማ እና አፋር የልማት ኮሪደሮች ለልማቱ የሚውል መሬት ለመለየት ኤጀንሲው ከክልሎቹ ጋር በጋራ በመሆን የታቀደ ቢሆንም እስካሁን ድረስ የመለየት ስራው ያልተከናወነ መሆኑ እና በኦዲቱ በታዩ ክልሎች በሁሉም ኤጀንሲው ለኢንቨስትመንት የተለዩ የልማት ቦታዎች መኖራቸውን በተለያዩ ሚዲያዎች ሆነ በድረገፅ ያላስተዋወቀ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

29. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በኦሮሚያ ክልል ባብዛኛው የተሰጡ መሬቶች ኤጀንሲው ከመቋቋሙ በፊት ጥናት ሳይደረግባቸው የተሰጡ መሆናቸው፣ በአሁን ሰዓት ግን በክልሉ ለልማቱ የተለዩ መሬቶችን ኤጀንሲው በማስጠናት አመቺ የሆኑትና ያልሆኑት የተለየ መሆኑን፣ አማራ ክልል ለልማቱ አመቺ የሆነውን መሬት ለይቶና አስጠንቶ ለኤጀንሲው የሰጣቸው መሆኑን፣ በትግራይና በደቡብ ክልል ለልማቱ የሚውሉ መሬቶች ለይተው ለኤጀንሲው የተሰጡ ቢሆንም ጥናት ያልተደረገባቸው መሆኑ፣ በድሬድዋ፣ በጅማ እና በአፋር ክልሎች የልማት ኮሪደሮች በጥናት ለልማቱ የሚውሉ መሬቶች ያልተለዩ መሆናቸውን ገልፀው ስለተለዩ መሬቶች በስፋት የማስተዋወቅ ስራ በበቂ ሁኔታ ያልተሰራበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

30. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በአማራ ክልል በወቅቱ በመሬት ባንክ ተይዞ የነበረው 561 ሄ/ር ብቻ መሆኑ፣ ከዚህ በስተቀር ለልማቱ የተለየው መሬት አሁንም በአርሶአደሮች ይዞታ ስር የሚገኝና ወደፊት ካሳ ተከፍሎበት ወደ መሬት ባንክ እንደሚገባ የሚጠበቅ እና ይህ መረጃም በክልሉ በኩል ተጠንቶ የቀረበ መሆኑ እንዲሁም ተጨማሪ የማመሳከሪያ ጥናት በኤጀንሲው በኩል እየተካሄደ እንዳለ፣ በሀዋሣና አርባምንጭ ኮሪደር የተገለጸው መሬት የመጀመሪያ ደረጃ መሬቱን የመለየት ጥናት የተካሄደ ሲሆን ለልማቱ ከተለየው መሬት ውስጥ ከኔዘርላንድ ኤምባሲ ጋር በመቀናጀት በይርጋለም የተስማሚነት ጥናት ተካሂዶ በክልሉ በኩል የከርሰ ምድር ውሀ ቁፋሮ የተጀመረ ሲሆን በትግራይ ክልል ከባለሀብቶች ጋር በመተባበር የተስማሚነት ጥናት በመካሄድ ላይ መሆኑ፣ በሀዋሳ አርባምንጭ ኮሪደር የመግባቢያ ሰነዱ ረቂቅ ለክልሉ መስተዳድር ቀርቦ ግብረመልስ እየተጠበቀ የሚገኝ መሆኑ፣ በጅማና

በድሬዳዋ ኮሪደር ለልማቱ የሚውል መሬትን የመለየት ሥራ ተካሂዶ የተስማማኒት ጥናት በድሬዳዋ ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ለማዋል ጥናቱ የተጀመረ መሆኑ፣ የአፋር ኮሪደር እስከአሁን በልማት ኮሪደርነት ያልተያዘ መሆኑ፣ የማስተዋወቅ ሥራው በሚሲዮኖቻችንና በየወቅቱ በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች ላይ የተከናወነ መሆኑ፣ በተጨማሪም በቀጣይ ኤጀንሲው በራሱ ድረ-ገጽ ለማስተዋወቅ በዝግጅት ላይ መሆኑ፣ በተለያየ መንገድ ባለሀብቶች በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ለመሰማራት ሲፈልጉ መሬት በተዘጋጀላቸው የልማት ኮሪደሮች የማስተዋወቅና የማስገባኘት ሥራ ተከናውኖ ወደ ልማቱ በመግባት ላይ መሆናቸው(ለምሳሌ በትግራይ የስፔን ኩባንያ - ኮምፔር ዋይ ኮምፔር 1200ሄ/ር፣ በሱማሌ ክልል -የእስራኤል ኩባንያ 3000ሄ/ር፣ በኦሮሚያ ክልል የኩዌት ኩባንያ - 168 ሄ/ር እና የሀገር ውስጥ ባለሀብት-100ሄ/ር ወዘተ... ) ገልፀዋል፡፡

31. ስለሆነም የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር በጋራ በመሆን በየክልሉ የሚገኘውን ለልማቱ አመቺ የሆነውን መሬት በመለየትና በማጥናት የማስተዋወቁ ስራ በስፋት ባለመከናወኑ የባለሀብቶችን አቅም ያላገናዘበ መሬት በመሰጠቱ የመሬት ዕጥረት እንዲከሰትና ኤክስፖርት ማድረግ እንዳይቻል አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ወደልማት ከመግባታቸው በፊት የአዋጭነት ጥናት ማቅረባቸውን በተመለከተ፤

32. ኤጀንሲው በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ለአዋጭነት ጥናት የሚያግዙ መረጃዎች ሊያሰባስብ፣ ሊያደራጅ እና በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች በቀላሉ ሊያገኙት በሚችሉበት መንገድ ሊያቀርብ ይገባል፡፡በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ የሚገቡ ባለሀብቶች ወደልማት ከመግባታቸው በፊት የአዋጭነት ጥናት ሊያቀርቡና በኤጀንሲው ባለሙያዎች ሊገመገም ይገባል፡፡

33. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ለአዋጭነት ጥናት የሚያግዙ መረጃዎች በመሰብሰብና በማጀራጀት ለባለሃብቶች ያላሰራጨ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በባለሃብቱ የሚቀርቡ የአዋጭነት ጥናቶችን ለመገምገም የሚያስችል መመሪያና የመገምገሚያ መስፈርት የተዘጋጀ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት 14 የአትክልትና ፍራፍሬ ባለሀብቶች ውስጥ ከአንዱ ካምፓኒ(ዩኒ ፍሩት ኃ/የ/የግ/ኩባንያ) በስተቀር በሌሎቹ የአዋጭነት ጥናት ያላቀረቡ መሆኑ እንዲሁም የአዋጭነት ጥናት ያቀረበው ድርጅትም ያቀረበው የአዋጭነት ጥናት ደረጃውን የጠበቀ፣ አዋጭነቱ አስተማማኝ የሆነና ጥናቱ ሊተገበር የሚችል ስለመሆኑ በኤጀንሲው ተገምግሞ የፀደቀ ስለመሆኑ የሚገልፅ መረጃ የካምፓኒው ፕሮፋይል በተከለሰበት ወቅት ያልተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

34. ስለጉዳዩ የሆርቲካልቸር ልማት የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለአዋጭነት ጥናት የሚያግዙ መረጃዎች በኤጀንሲው በሰነድ ደረጃ በማዘጋጀት

ባለሃብቶች ሲመጡ መረጃውን የምንሰጣቸው ሲሆን መረጃዎችን ተደራሽ በማድረግ ረገድ በድረገፅ ወይም በመረጃ መረብ ያልተደራጀ ሲሆን ምክንያቱም ሌሎች አካላት መረጃውን አለአግባብ እንዳይጠቀሙት ለመከላከል ሲሆን ወደፊት መረጃውን በማዳበር በመረጃ መረብ ላይ እንዲለቀቅ የሚሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው ከመቋቋሙ በፊት በክልሎች መሬት የሚሰጥ የነበረ እና ቢዝነስ ፕላናቸውም እዛው ተገምግሞ የሚቀመጥበት አሰራር የነበረ ሲሆን የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ከተቋቋመ በኃላ ከኦሮሚያ ክልል ጋር በጋራ ለመስራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመው ከ2005 ወዲህ የመገምገሚያ ሰነድ በማዘጋጀት በጋራ በመገምገም የመሬት አሰጣጥ ሂደቱ በመከናወን ላይ የሚገኙ ሲሆን ከ2005 ዓ.ም በኃላ መሬት የወሰዱ ባለሀብቶች ቢዝነስ ፕላናቸው በኤጀንሲው በሚገኘው ፋይላቸው ውስጥ የሚገኝ መሆኑን እና በሌሎቹ ክልሎች የሚሰማሩ ባለሃብቶች ከሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ጋር በጋራ ለመስራት የተፈራረሙት የጋራ ሰነድ ባለመኖሩ ክልሎቹ በራሳቸው የሚያከናውኑ መሆኑን፣ ማስረጃው(የአዋጭነት ሰነዱ) ኤጀንሲው በያዘው የካምፓኒ ፕሮፋይል ውስጥ የማይገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡

35. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ በነባራዊ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የማስተዋወቅ ሥራው ከሆርቲካልቸር ማሕበር ጋራ በመሆን በመካከለኛው ምስራቅ ባለሀብቶችን ለመሳብ በሀገራችን በየሁለት ዓመቱ በሚዘጋጀው ዓለምአቀፍ ኤግዚቢሽን እንዲሁም በውጭ ሀገራት በየወቅቱ በሚዘጋጁ ሌሎች ኤግዚቢሽኖች ላይ የተከናወነ መሆኑ፣ በተጨማሪም በቀጣይ ኤጀንሲው በራሱ ድረ-ገጽና በተለያዩ ሀገራት የሚዘጋጁ የተመረጡ ኤግዚቢሽኖች በመለየት ለማስተዋወቅ በዝግጅት ላይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

36. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ለአዋጭነት ጥናት የሚያግዛቸው መሰረታዊ መረጃዎች በተደራጀና ተደራሽ በሆነ መልኩ ያልተደራጀ በመሆኑ መረጃዎቹን ለማሰባሰብ ጊዜ የሚያባክኑ መሆኑ እና በባለሃብቶች የሚዘጋጀው የአዋጭነት ጥናት የተሳሳተ እንዲሆንና ባለሀብቶች ውጤታማ እንዳይሆኑ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡

## ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ለባለሀብቶች በወቅቱ እንዲሟላላቸው የተዘረጋ ስርዓትን በተመለከተ፤

37. ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬትና የግንባታ ፋቃድ እንዲያገኙ እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶችን (ውኃ፣ መብራት፣ ስልክ፣ መንገድ ወዘተ) እንዲሟላላቸው ድጋፍና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሰርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

38. ኤጀንሲው ከኦሮሚያ ክልል ጋር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬትና የግንባታ ፋቃድ እንዲያገኙ የሚመቻችበት እና አፈፃፀሙን በቅርበት ክትትል የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ በመተግበር ላይ የሚገኝ ቢሆንም በተለይም በመሬት አቅርቦት በኩል በክልል፣ በዞንና በወረዳ የሚገኙ ኃላፊዎች እርስ በእርስ ተናበውና ተግባብተው የማይሰሩ መሆኑ፣ መመሪያ ሲወጣ ወይም ውሳኔ ሲሰጥ አፈፃፀሙ ደካማ መሆኑ፣ ኤጀንሲው (ከኦሮሚያ ክልል ውጪ) ከሌሎቹ ክልሎች ጋር የጋራ ስምምነት ባለመኖሩ የመሬት አሰጣጥ ሂደቱንና አፈፃፀሙን ክትትልና ድጋፍ የማያደርግ መሆኑን፣ በአጠቃላይ የመሬት አሰጣጥ ስርዓቱ ቀልጣፋ ያለመሆኑ መረጃ በተከለሰበትና በቃለመጠይቅ ወቅት ታውቋል፡፡

39. ዘ-ጊቪንግ ትሪ ነርሰሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እንደተገለፀው ካምፓኒው የማምረት ስራ እየሰራ የሚገኝ ቢሆንም የሀገር ውሰጥና የውጪ ደንበኞቻቸውን ለማግኘት ኢንተርኔት ማግኘት ያልቻሉ በመሆኑ ስራቸው ላይ መሰናክል የፈጠረባቸው መሆኑ፣ በአጠቃላይ የመሰረተ ልማት(የመንገድ፣ የኃይል መቆራረጥ) ችግር ያለባቸው መሆኑ፣ እነዚህ ችግሮች በሌሎች ኩባንያዎችም(ለምሳሌ የላይኛው አዋሽ፣ ጄቱ፣ ጆይ ቴክ፣ ሉና፣ ግሪን ማርክ ኸርብስ፣ አልሜታ ኢምፔክስ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያዎች) ያሉ መሆናቸው፣

40. በኤጀንሲው የሰኔ ወር የ2006 የመስክ ሪፓርት ላይ እንደተገለፀው በመርቲ ወረዳ ላይ ለተሰማሩ ኩባንያዎች(ዘ-ጊቪንግ ትሪ ነርሰሪ እና የላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ) የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ላይ እጥረት ያለ መሆኑ፣

41. አልሜታ ኢምፔክስ ኃ/የተወሰነ የግል ኩባንያ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሲዳማ ዞን ወንዶ ጢቃ በሚባል ቦታ 500ሄ/ር ከመንግስት ተረክቦ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማግኘት በመጋቢት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የጠየቀ ሲሆን የኢትዮጲያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ለእርሻው አገልግሎት የሚውል 351.28ኪ.ዋ የኃይል ጥያቄ በተጠየቀው መሰረት የዕቃና የእጅ ስራ ዋጋ 1,743,356.12 ብር እንድንከፍል የተጠየቀ ቢሆንም የተጠየቀውን የዋጋ ግምት በሦስት ዓመት የክፍያ ጊዜ መክፈል የሚቻልበት ሁኔታ እንዲመቻችላቸው በየጊዜው(ከ2001-2005ዓ.ም) ቢጠይቁም እንዲህ ዓይነት አሰራር እንደሌለ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በየወቅቱ ምላሽ የተሰጣቸው ሲሆን በ29/02/2006ዓ.ም ላይ ለመስመሩ ዝርጋታ 1,882,752.49 የተጠየቁትን ብር ለመክፈል ኩባንያው በመወሰን ክፍያ የፈፀሙ ቢሆንም እስካሁን ድረስ የመብራት ኃይል ዝርጋታው ያልተጠናቀቀ መሆኑ፣

42. ፓም ጎልድ ፍሩትስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እ.ኤ.አ በጥር 3,2012 ለሆርቲካልቸር ኤጀንሲ በተፃፈ ደብዳቤ እንደተገለፀው የሚያስፈልገውን የኃይል ፍላጎት ለማሟላት ለኢትዮጲያ ኤሌክትሪክ ኃይል መቀሌ ቅርንጫፍ ባቀረበው መሰረት 618,952.33 ብር እንዲከፍል በተገመተው ግምት መሰረት ሙሉ በሙሉ ክፍያ ቢፈፅምም አገልግሎቱን እስከሁን ድረስ ማግኘት ያልቻለ መሆኑ፣

43. በኤጀንሲው የመስከረም ወር የ2005 እቅድ አፈፃፀም ሪፓርት ላይ እንደተገለፀው በላይኛው አዋሽ አካባቢ የሚገኙ ኩባንያዎች (ዘጊቪንግ ትሪ፣ የላይኛው አዋሽ እና አዳዲስ ኩባንያዎች)

በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ የመንገድ ብልሽት በመኖሩ በከፍተኛ ደረጃ ስራቸውን መስራት ያልቻሉ መሆናቸው፣

44. በድሬደዋ የልማት ኮሪደር የትራንስፓርት፣ የመንገድ እና የመብራት መሰረተ ልማቶች ያልተሟላ መሆኑ እና ከድሬደዋ ጅቡቲ የሚያገናኘው መንገድ ደረጃውን የጠበቀ አለመሆኑ፣
45. በመርቲ አካባቢ የሚገኙ 3 ኩባንያዎች የመስመር ዝርጋታና የትራንስፎርመር ጥያቄ አቅርበው ከአመት በላይ ያልተስተናገዱ መሆናቸው፣
46. በሰበታ አካባቢ የሚገኙ 5 ኩባንያዎቹ ከፍተኛ ቮልቴጅ ያለው ትራንስፎርመር እንዲገዙ ቢደረግም ከdomestic መስመር ጋር በመገናኘታቸው የኃይል መቆራረጥ ያለባቸው መሆኑ፣
47. በሆለታ፣ ዝዋይና ቢሾፍቱ አካባቢዎች ከፍተኛ የኃይል መቆራረጥ በመኖሩ በመሳሪያዎች ላይ ብልሽት እያስከተለ መሆኑ(ዩኒ ፍሩት፣ ጂቱ)፣ ኦዲቱ ሲከናወን ማስረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
48. በናሙና የተመረጡ ኩባንያዎች በቃለመጠይቅ ወቅት እንደገለፁት ኤጀንሲው በወቅቱ የመሰረተ ልማት አገልግሎት ( ውኃ፣ መብራት፣ ስልክ፣ መንገድ ወዘተ) እንዲያገኙና ለግንባታ ከውጪ ሀገር የሚገዙ ግብአቶች እንዲገቡ እንዲሁም ከሀገር ውስጥ የሚገዙ ግብአቶች በወቅቱ እንዲቀርቡ የድጋፍ ደብዳቤ የሚፅፍ ቢሆንም አፈፃፀሙ ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየት በኤጀንሲው ደረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን መፈታት የሚችለውን እንዲፈታ መፈታት ያልቻሉትን ችግሮች በማጥናት ለሚመለከተው የበላይ አካል በማቅረብ እንዲፈታ ጥረት የሚያደርግ ቢሆንም ተከታትሎ አፈፃፀሙን ክትትል ማድረግ ላይ ክፍተቶች መኖራቸው፣
49. ስለጉዳዩ የሆርቲካልቸር ልማት የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ከኦሮሚያ ክልል ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬትና የግንባታ ፋቃድ እንዲያገኙ የሚመቻችበት እና አፈፃፀሙን በቅርበት ክትትል የሚደረግበት የአሰራር ሰርዓት ዘርግቶ በመተግበር ላይ የሚገኝ መሆኑን ከሌሎቹ ክልሎች ጋር ግን ገና በጋራ ለመስራት ጥረት እየተደረገ መሆኑን በተጨማሪ በአሁን ወቅት ብዛት ያለው ባለሀብት ወደ ዘርፉ ለመግባት ፍላጎት እያሳዩ መሆናቸው በተቃራኒ የመሬት አቅርቦቱ በጣም ውስን በመሆኑ ክልሎች የመሬት አቅርቦት ላይ በተሻለ መስራት የሚጠበቅባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

- ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ በነባራዊ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ከኦሮሚያ ክልል ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ከላይ እንደተገለፀው ሆኖ በዞንና በወረዳ ደረጃ ያለውን የአፈፃፀም ችግር በተመለከተ ከክልሉ ጋር በተዋቀረው የጋራ ኮሚቴ አመራር እየተሰጠበት በየወቅቱ የተወሰዱ እርምጃዎች በቃለ-ጉባዔ ተይዘው የሚገኙ መሆኑ፣ ሌሎች ክልሎችን በተመለከተ ቋሚ መድረክ ባይኖርም እንደአስፈላጊነቱ ችግሮችን በወቅቱ ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት የሚደረግ መሆኑ፣ የመሬት አሰጣጡን ቀልጣፋ ለማድረግ የአሰራር ማንዋል ተዘጋጅቶ ባለድርሻ

አካላት አስተያየት እንዲሰጡበት ለክልሎች የተላከ መሆኑ፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦትን በተመለከተ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር ቋሚ የጋራ መድረክ ያለ ሲሆን በተለይ ከቴሌና ከኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ጋር በተያያዘ የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀትና የጋራ በማድረግ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ዩቲሊቲ በኩል የሚሰጠው አገልግሎት ውሱንነት እንደተጠበቀ ሆኖ  አንዳንድ ጊዜም ባለሀብቶቹ ግዴታቸውን በወቅቱ መወጣት ሳይችሉ ሲቀር ከመዘግየቱ በስተቀር የጋራ ጥረቱ ቀጣይነት ያለው መሆኑ፣ በመርቲ አካባቢ የተገለጸውን የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ችግርን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስፈልጉ ግንባታዎችን ለማካሄድ የሚያስፈልገው በጀት በአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን በኩል ቀርቦ ተጠቃሚዎች የግንባታውን ወጪ ለመጋራት ኮሚቴ ተቋቁሞ በስራ ላይ የሚገኝ መሆኑ፣ አልሜታ ኢምፔክስን በተመለከተ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲያገኝ በኤጀንሲው በኩል ድጋፍ ተደርጐለት ክፍያውን እንዲፈፅም ተገልፆለት በወቅቱ ባለመክፈሉ የተከሰተ ችግር መሆኑ፣  ዘ-ጊቪንግ ትሪ ነርሰሪ በኤጀንሲው ድጋፍ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲያገኝ የተደረገ ሲሆን የኢንተርኔት አገልግሎትም እንዲያገኝ አማራጭ ቴክኖሎጂዎች ቀርበውለት የተሻለውን አማራጭ ለመጠቀም የአቅም ውስኑነት የነበረበት መሆኑን በመግለጽ  በአነስተኛ ቴክኖሎጂ እየተጠቀመ የሚገኝ መሆኑ፣ በሌሎች አካባቢዎችም ላይ ጥናት የተካሄደ ሲሆን የተሻለ የፋይበር ኦፕቲክስ አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ እየተመቻቸ የሚገኝ መሆኑ(ለምሳሌ በቆቃና በቢሾፍቱ)፣ ፖም ጐልድ የተባለው ኩባንያ ኤጀንሲው በተከታታይ ባደረገው ጥረት የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጐቱን ለማሟላት ትራንስፎርመር እንዲያገኝ የተደረገ መሆኑ፣ በላይኛው አዋሽ አካባቢ የሚካሄደውን ልማት በተመለከተ ኤጀንሲው ከፌዴራል የመንገዶች ባለስልጣን ጋር በመነጋገር በመንገድ ፈንድ ተካቶ ሥራው ለማከናወን በዕቅድ መያዙን በጽሁፍ ያሳወቃቸው እና ክትትል እየተደረገ የሚገኝ መሆኑ፣ በአርባምንጭ የእርሻ ልማቶችን ያጋጠማቸው የውሃ ችግርን በተመለከተ በኤክስፖርት ላይ እየተሳተፉ ባለመሆኑ በቂ ክትትል እየተደረገ ባይሆንም በቀጣይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚታይ መሆኑ፣ የድሬዳዋ የልማት ኮሪደርን ለማጠናከር በፌዴራል መንግስት ደረጃ የተጀመረው የባቡር መስመር ግንባታ ሲጠናቀቅ የሚፈታ መሆኑ፣ በሀገራችን ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት አቅም ውሱንነት እንደተጠበቀ ሆኖ በመርቲ፣ በሰበታና በሆለታ አካባቢ ያለውን የመስመር ዝርጋታና የሃይል መቆራረጥ ችግርን ለመፍታት ከላይ እንደተገለፀው ጥረት እየተደረገ ሲሆን የመስመር ዝርጋታ ክፍያ በመፈፀማቸው አገልግሎቱን ያገኙ ኩባንያዎችም እንዳሉ ገልፀዋል፡፡

50. የመሠረተ ልማት አቅርቦት ችግርን በተመለከተ ኤጀንሲው በየወቅቱ በጋራ መድረኮች ችግሮችን ለመፍታት ደረጃ በደረጃ ከሚያደርገው ጥረት ባሻገር ጐልተው የሚታዩ ችግሮችን በተመለከተ በየወሩ ለብሔራዊ ኤክስፖርት አስተባባሪ ካውንስል ለውሳኔ በማቅረብ አቅጣጫ ይሰጣል፡፡

51. በመቀጠልም በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች በወቅቱ የመሰረተ ልማት አገልግሎት ( ውኃ፣ መብራት፣ ስልክ፣ መንገድ፣ ወዘተ)  እንዲያገኙ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን

ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሟላላቸው ኩባንያዎች መኖራቸው፣ እንዲሁም ችግሮች ለመፍታት በየጊዜው ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በስልክ፣ በደብዳቤ ብሎም በአካል በመገኘት በመነጋገር ለመፍታት ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልፀው በአጠቃላይ የኃይል መቆራረጥን ለማስቀረት የዶሜስቲክና የኢንዱስትሪ መስመር ሊለይ የሚገባ መሆኑና ከባለሀብቶች የሚነሱ ችግሮችን በአጭር ጊዜ ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

52. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች የመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦቶች በወቅቱ እንዲሟላላቸው ጥረቶች ቢኖሩም አፈፃፀም ላይ ችግር በመኖሩ ባለሀብቶች ላላስፈላጊ ወጪ እና ወደዘርፉ ፈጥነው እንዳይገቡ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስ...ወዘተ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

53. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስ አገልግሎቶችን እና የባለሀብቶችን የካፒታል አቅም ለማጎልበትና ወደ ልማት በአፋጣኝ እንዲገቡ ለማድረግ ባለሀብቶች ከፋይናንስ ተቋማት የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

54. በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሃብቶች በገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን የሚሰጠው አገልግሎት ቀልጣፋ ያለመሆኑ፣ የሀገሪቱ የውጪ ምንዛሬ እድገት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ትላልቅ ባለሀብቶች(ሞዴል የሆኑ የአትክልትና ፍራፍሬ ኩባንያዎች) ተለይተው የሚስተናገዱበት አሰራር ያለመኖሩ፣ የልማት ባንክ ከሌሎች ባንኮች ጋር ተቀናጅቶ የማይሰራና የብደር ጥያቄ ሲቀርብ ለመወሰን ረጅም ጊዜ የሚወስድ መሆኑ እንዲሁም በባንክና ጉምሩክ መካከል የሚካሄደው የኤክስፓርት መረጃ ፍሰት ወቅታዊ፣ ተመሳሳይ፣ ትክክለኛና ያልተሟላ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

55. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በጉምሩክ ያለው አሰራር ቀልጣፋ ያለመሆኑ እንዳለ ቢሆንም በአብዛኛው የመጓተት ሁኔታዎች የሚፈጠረው ባለሀብቶቹ የተሟላ መረጃ ባለማቅረባቸው መሆኑን፣ ይህን ችግር ለመፍታት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በየ15 ቀኑ የሚገናኙበት አሰራር በመዘርጋት ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በመቀጠልም ብድርን በተመለከተ ባንኩ የራሱ የአሰራር መመሪያ ያለው መሆኑና ባለሀብቶች አስፈላጊውን መረጃ አሟልተው እስከቀረቡ ድረስ አገልግሎቱን የሚያገኙ መሆኑን፣ በተጨማሪም ኤጀንሲው የልማት ባንክ የቦርድ አባል በመሆኑ ከባለሀብቶች የሚነሱ ችግሮችን በማቅረብ መፈታት የሚችሉትን እንዲፈቱ ጥረት የሚያደርግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሞዴል የሆኑ ባለሀብቶችን በተመለከተ ለይቶ

የተፋጠነ አገልግሎት እንዲያገኙ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያስተላለፈና ስማቸውም የተለጠፈ መሆኑን እና አገልግሎቱን አላገኙሁም ብሎ ቅሬታ ያስገባ ባለሀብት ያለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

56. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ከባለሀብቶች በየጊዜው የሚነሱ ችግሮች ለመፍታት ለሚመለከታቸው አካላት የድጋፍ ደብዳቤ ከመፃፍ በዘለለ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በአፋጣኝ መፍትሂ እንዲያገኙ ጥረቶች ቢኖሩም የተጠናከሩ አለመሆናቸው፣ በተጨማሪም ኤጀንሲው በቅርበት ሞዴል የሆኑት ባለሀብቶች ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆናቸውን ክትትል ሊያደርግ የሚገባ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

57. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ቅንጅታዊ ሥራን ለማጠናከር ሲባል የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የልማት ባንኩ የቦርድ አባል ሆነው በመስራት ላይ የሚገኙ ሲሆን ከብድር ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ችግሮችም በየወቅቱ ምላሽ እንዲያገኙ እንደሚደረግ(ለምሳሌ ችግሩ የተፈታለት ኤታምኮ ኩባንያ) ከዚህ በተጨማሪ ለልማቱ ማስፋፊያ የሚውል ብድር ከልማት ባንክ እንዲያገኙ በቂ የብድር በጀት የተያዘ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

58. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ባለሀብቶች የተቀላጠፈ የባንክ፣ የጉምሩክ፣ የብድር፣ ወዘተ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ዘርፉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ችግሮችን በአፋጣኝ መፍታት ባለመቻሉ የኤጀንሲው የማስፈፀም አቅም ፈታኝ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

## የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ ማድረጉን በተመለከተ፤

59. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ከፌደራልና ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

60. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅቶቹ ለልማቱ የሚያስፈልጋቸውን የሰው ኃይል በማስተባበርና በሟሟላት ድጋፍ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባሯዊ ያላደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተደረጉ ቃለ መጠይቶችና ከተከለሱ ማስረጃዎች ታውቋል፡፡

61. የሆርቲክልቸር ልማት የኤጀንሲ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ዘርፉ ብዙ የሰው ጉልበት የሚፈልግ በመሆኑ የሰራተኛ ችግር የገጠማቸው ድርጅቶችን ጥያቄ ሲያቀርቡ ከኦሮሚያ ክልል ጋር በጋራ የሚሰራበት አሰራር መኖሩን ገልፀዋል፡፡ይሁን እንጂ በሁሉም ክልሎች በጋራ የመስራቱ ሁኔታ ያልተጠናከረ በመሆኑ ድጋፉ መስጠት ያልተቻለ መሆኑን እና ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት የድርጅቶቹን ዕቅድና አቅም በማገናዘብ ድጋፍ መስጠት ሲገባቸው ገና ጥያቄ ሲቀርብ የምንሰራው በማለት የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

62. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ከፌደራልና ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር አትክልትና ፍራፍሬ ልማቶችን ለድርጅቶቹ አንቀሳቃሽ ሞተር ተደርጎ የሚወሰደው የሰው ኃይል እንዲሟላ ባለመደረጉ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ፈጥነው ወደ ልማቱ እንዳይገቡ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

## የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉና ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በአግባቡና በወቅቱ ለታቀደላቸው አላማ መዋላቸውን በተመለከተ፤

63. ኤጀንሲው ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉና ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች እና የተሰጡ ድጋፎች በአግባቡና በወቅቱ ለታቀደላቸው አላማ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ክትትል የሚያደረግበት ስርዓት መዘርጋቱን እንዲሁም መሬት ወስደው ወደ ልማት ያልገቡ ባለሀብቶች በአግባቡ ተለይተው በአፋጣኝ ወደ ልማት እንዲገቡ ካልሆነም እርምጃ የሚወሰድበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

64. ከ2003-2006 ዓ.ም በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፉ ከተሰማሩ 38 ባለሀብቶች ውስጥ 11 ባለሀብቶች ወደ ልማት ያልገቡ መሆናቸው፣ 17 ባለሀብቶች የሚያመርቱትን ምርት ለውጪ ገበያ የማያቀርቡ መሆናቸው፣ አጠቃላይ በአትክልትና ፍራፍሬ ለባለሀብቶቸ ከተላለፈ መሬት (16,756 ሄክታር) የለማው እስከ 2006 ዓ.ም 11,517 ሄክታር (69%) ብቻ መሆኑ፣ ለሙዝ ለአውት ግሮዎር አምራቾች 10,000 ሄክታር መሬት ሁሉም የሚለማ ቢሆንም የሙዝ ምርት ለውጪ ገበያ የማይቀርብ መሆኑ እንዲሁም ወደ ልማት ከገቡት 27 ባለሀብቶች ውስጥ ደግሞ 17 ባለሀብቶች የሚያመርቱትን ምርት ለውጪ ገበያ የማያቀርቡ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡ (ሰንጠረዥ 1)

| የምርት ዓይነት (Type) | በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች (2003-2006) ብዛት | የዕቅድ ክፍለ ጊዜ | | እስከ 2006 ዓ.ም የለሙ መሬቶች (Developed land till 2006)(ha) | ወደ ልማት ያልገቡ ባለሀብቶች እስከ 2006ዓ.ም በቁጥር | ምርታቸውን ወደ ውጪ(Export) የማይልኩ ኩባንያዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በስትራቴጂክ ዕቅድ መሬት በሄክታር | የተላለፈ መሬት በሄክታር እስከ 2006 | | | |
| አትክልት (Vegitables) | 29 | 11,540.3 | 4,552 | 809(18%) | 11 | 12 |
| ፍራፍሬ (Fruits) | 9 | 11,500.1 | 2,204 | 708(32%) | - | 5 |
| | | | 10,000.0(አውትግ ሮዎር(ሙዝ) | 10,000.0(100%) | - | - |
| ድምር(Sum) | 38 | 23,040.4 | 16,756 | 11,517(69%) | 11 | 17 |

*ሰንጠረዥ1፡- ከ2003-2006 በጀት ዓመት ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የዋለ መሬት አፈፃፀም*

- ✓ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ከኦሮሚያ ክልል በስተቀር ከሌሎች ክልሎች ጋር በጋራ ለባለሀብቶች የተሰጡ መሬቶች ለታለመለት ዓላማ መዋላቸውን ክትትል የሚያደርግበት አሰራር የሌለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ታውቋል፡፡ ለአብነት ያህል አንዳንድ አዳዲስ እርሻዎችም ሆነ ነባር እርሻዎች (ለምሳሌ አልሜታ ኢምፔክስ ወንዶ ጢቃ፣ በሀዋሳ ሜትሮላክስ፣ ዳንዲ ቦሩ፣ ታም አግሪካልቸር፣ አደም ሆርቲካልቸር፣ ኢታምኮ፣...) የኤክሰፓርት አትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎች ለማምረት እና ኤክስፖርት ለማድረግ ውል ቢገቡም ለሀገር ውሰጥ ገበያ የሚያቀርቡ እና ከውል ውጪ የሚያመርቱ መሆኑ፣

65. የጥር ወር የ2006 የመስክ መልስ ሪፓርት ላይ እንደተገለፀው ኩባንያው/ኦሜጋ ፋርም / የተለያዩ አትክልቶችን በማምረት እና ኤክስፓርት የሚያደርግ የነበረ ሲሆን ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የኤክስፓርት ስራውን ያቋረጠ መሆኑ በጉዳዩ ላይ ኤጀንሲው የወሰደው እርጃ ያለመኖሩ፣
66. በ2006 በጀት ዓመት ወደ ልማት እንዲገቡ እቅድ የተያዘላቸው 18 ኩባንያዎች ሁሉም በእቅዳቸው መሰረት አልምተው ወደ ኤክሰፓርት ያልተሸጋገሩ መሆናቸው፣
67. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ከኦሮሚያ ክልል ጋር በጋራ በተጠናከረ መልኩ እየተሰራ እንደሚገኝ፣ ሀገሪቷ ከልማቱ ማግኘት ያለባትን ገቢ እንዳታጣ ባለሀብቶች ከውሉ ውጪ ሲያመርቱ በማስታመም እንዲታረሙ ከማድረግ እና ምርታማነታቸውን እንዲጨምሩ ከመደገፍ አንፃር ዘርፉ እስኪጠናከር ድረስ እየተሰራ መሆኑን፣ አማራ ክልል ከባለሀብቶች መሬት ሲነጥቅ (እርምጃ ሲወስድ) ለኤጀንሲው የሚያሳውቅ መሆኑን፣ ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርቡ ባለሀብቶችን በተመለከተ የሀገር ውስጥ ገበያው ኤክስፖርት ከሚያደርጉበት ዋጋ የተሻለ በመሆኑ ይሄ ችግር ሊከሰት የቻለ መሆኑን፣ ነገር ግን ኤክስፖርት እናደርጋለን በማለት ስለሆነ የተለያዩ ድጋፎችን ማግኘት የቻሉት ኤክስፖርት ማደረግ ያለባቸው በመሆኑ በቅርበት ክትትል በማድረግ ወደ ኤክስፖርቱ እንዲመለሱ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
68. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ወደ ልማት ያልገቡ ባለሀብቶችን በተመለከተ ምክንያቶቻው በኩባንያዎች የውስጥ ማኔጅመንት ችግር፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ልምድ ማነስ፣ የባንክ ብድር ፎርማሊቲዎችን ባለማሟላት፣ የሀይል አቅርቦት በወቅቱ ባለማግኘት፣ በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ባለማምረት፣ የኢንቨስትመት ዘርፍን ከአትክልት ወደ አበባ ወይም ከአበባ ወደ አትክልት በመቀየር የመነጩ ሲሆን እንደችግሮቻቸው አግባብ መፍትሄ ለመስጠት ጥረት የሚደረግ መሆኑ፣ በአርባ ምንጭ አካባቢ የሚመረተውን ሙዝ ኤክስፖርት ለማድረግ በተለያዩ ጊዜያት የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ጥረት ተደርጎ ለሳዑዲ ገበያ ምርት የመላክ ስራ ተቋርጦ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ኤክስፖርቱን ለማስቀጠል የገበያ ትስስር የተፈጸመ ሲሆን ኤክስፖርቱ በቅርቡ እንደሚጀመር የሚጠበቅ መሆኑ፣ ምርቱን በዘላቂነት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሎጂስቲክ ችግር ያለ በመሆኑ ከባቡር መስመር ዝርጋታ ጋር ተያይዞ የሚፈታ መሆኑ፣ ከኦሮሚያ ውጭ ባሉ ሌሎቹ ክልሎች በክልሉ መስተዳድር

በኩል የሚወሰደው እርምጃና የመረጃ ልውውጥ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀጣይ የሚኖረው ክትትል የመግባቢያ ሰነድ ሲፈረም የሚከናወን እንደሚሆን፣ ከሆርቲካልቸር ምርት ውጭ የሆነ ሰብል አምርተው የተገኙት ከክልሉ ጋር በጋራ በመሆን እንዲታረሙ ምክር የተሰጣቸው መሆኑ፣ የጥር ወር የመስክ ሪፖርትን መነሻ በማድረግ ኦሜጋ ፋርምን በተመለከተ እርሻው የኤክስፖርት ምርቶችን ሲያመርት ቆይቶ ያቋረጠበት ምክንያት ከንግድ ፈቃድ ዕድሳት ጋር በተያያዘ ኩባንያው የገለፀውን የካፒታል መጠን ማሳየት ባለመቻሉ ሲሆን ችግሩ  በንግድ ሚ/ር በኩል እንዲታይለት ድጋፍ  መደረጉን ገልፀዋል፡፡

69. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መሬት ወስደው ወደ ልማት ያልገቡ፣ በከፊል ያለሙ፣ ምርታቸውን ኤክስፖርት ማድረግ ያልቻሉ፣ ምርታቸውን ከዕቅድ በታች ኤክስፖርት የሚያደርጉ እና ምርታቸውን ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚቀርቡ ባለሀብቶችን በየደረጃው ድጋፍና ክትትል በማድረግ ሊሻሻሉ ያልቻሉትን ምክንያት በመለየት እርምጃ ሊወሰድ ካልቻለ በዘርፉና ከልማቱ ከውጪ ንግድ ይገኛል ተብሎ የተቀመጠው ገቢ እንዲታጣ ከማድረጉም በላይ  ወደ ዘርፉ ለመግባት የሚፈልጉ አዳዲስም ሆኑ የተሻለ አቅም ያላቸውና ለማስፋፋት የሚጠይቁ ነባር ባለሀብቶች መልማት የሚችል መሬት ያለአግባብ ጥቅም ላይ በመዋሉ ምክንያት የሚለማ መሬት እጥረት እንዲከሰት አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

**ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምርት እና ምርታማነትን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ስርዓት ዘርግቶ በአገር ውስጥ እና በዓለም ዓቀፍ ገበያ ጥራቱን የጠበቀ ተወዳዳሪ ምርት ለማምረት እንዲቻል የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤**

**የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በአትክልትና ፍራፍሬ በኮንትራት ልማት የሚሳተፉ አርሶ አደሮችን (አውቶግሮዎሮችን) በመመልመል  የስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፤**

70. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው  ከክልሎች ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሳተፉ የኮንትራት አርሶ አደሮች (አውቶግሮዎሮች) በመመልመልና በማደራጀት የስልጠናና የቴክኒክ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

71. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ  የኤክስፖርት ምርት ማምረት የሚችሉ የኮንትራት አርሶ አደሮችን (አውትግሮዎሮችን) ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ምቹ በሆኑ ክልሎች እንዲደራጁና ወደ ምርት እንዲገቡ እና ተከታታይነት ያለው የክህሎት ስልጠናዎችና የቴክኒክ ድጋፎችን በመቂ አካባቢ ላሉ አውትግሮዎሮች የሚያደርግ ቢሆንም በሌሎቹ አካባቢዎች ያልተስፋፋ መሆኑ፣ እንዲሆም የኮንትራት አርሶ አደሮች (አውትግሮዎሮች) ማበረታታት የሚችሉ የግብይት፣ የብድርና የሎጀስቲክስ መሰረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲሟላላቸው በበቂ ሁኔታ ድጋፍና ክትትል

የማያደርግ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አውቶግሮወር(የኮንትራት አርሶ አደሮች) በተመለከተ ለየት ያለ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ማለትም ቀን በቀን ከእርሻ እስከ ምርት ስብሰባ ድረስ ያለው ሂደት የሚረዳቸው ባለሙያ የሚያስፈልጋቸው መሆኑንም ይህን ስራ ሊያከናውን የሚችለው የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያ መሆኑን፣ ኤጀንሲው የንድፍ ሀሳብና የክህሎት ተከታታይ ስልጠና በመስጠት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ መሆኑን፣ በተጨማሪም ኤጀንሲው አውቶግሮዎሩንና ኤክስፖርት ማድረግ ከሚችለው ካምፓኒ ጋር በውል የሚተሳሰሩበትና በውሉ መሰረት እየተሰራ መሆኑ ክትትል የሚያደርግበት ሂደት መኖሩን፣ በተጨማሪም ካምፓኒው ከአውትግሮዎሩ ጋር ውል ከገባ በኃላ በውሉ መሰረት ለአውቶግሮዎሩ ሙያዊ ድጋፍና የግብዓት አቅርቦት እገዛ የሚያደርግ መሆኑን፣ በአጠቃላይ አውቶግሮዎሮችን ለማስፋፋት በአካባቢው የኤክስፖርት ገበያ ያለው ካምፓኒ ሊኖር እንደሚገባ፣ በቅርብ በቆቃ፣ በአምቦ፣ ሆለታ እና ባህር ዳር አካባቢ አውትግሮዎሮችን ለማደራጀት እየተሰራ እንደሚገኝ ይህም የሆነበት ባለሀብቶች በነዚህ አካባቢ ከአውትግሮዎርስ ጋር ተሳስሮ ለመስራት ፍላጎት ያሳዩ በመሆናቸው መሆኑን ገልፀዋል በተጨማሪም የተግባር ማሰልጠኛ ማዕከል መጠናከር ያለበት መሆኑን፣ ሞዴል የሆኑ አውቶግሮዎሮች ረዘም ያለ ስልጠና በማሰልጠኛ ማዕከል ማግኘት ያለባቸው መሆኑን ይህም ከበጀት ጋር የሚያያዝ በመሆኑ በኤጀንሲው ደረጃ እየተነጋገሩበት እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

73. ኤጀንሲው በሁሉም ክልሎች የሚገኙ አርሶ አደሮችን በማደራጀት እና በስልጠናና በቴክኒክ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በጥራትና በብዛት እንዲያቀርቡ እና ኤክስፖርት ከሚያደርጉ ባለሀብቶች ጋር በማስተሳሰር ወይንም በአውትግሮዎር ዩኒየን ደረጃ ምርታቸውን ኤክስፖርት እንዲያደርጉ የሚደረግበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ካልተደረገ ከፍተኛ የሆነ የምርት መጠንና ጥራት እንዲቀንስና በግብይት ወቅት ከፍተኛ የሆነ የምርት ብልሽትና ብክነት እንዲከሰት እና የውጪ ንግድና የምርት ተፈላጊነት እንዲቀንስ ከማድረጉም በላይ ሀገሪቱ ከኤክስፖርት ለማግኘት ያቀደችውን ገቢ እንዳይሳካ ያደርጋል፡፡

## የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን ውጤታማ የሚያደርጉ የምርት አመራረትና አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን በመሰብሰብና ማንዋሎች በማዘጋጀት በስልጠና እና ሰርቶ ማሳያ ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፤

74. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን ውጤታማ የሚያደረጉ ቴክኖሎጂዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር በመሰብሰብ ለባለሀብቶችና አውትግሮዎሮች (የኮንትራት አርሶ አደሮች) የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትና ምርት አያያዝ፣ የመሰኖ አጠቃቀም፣ የአግሮኖሚ እንክብካቤ፣ ዝሪያ አመራረጥ፣

ምርት አጠባበቅና፣ ሌሎች የአትክልትና ፍራፍ"ሬ ቴክኖሎጂ ፓኬጅ ያካተተ ማንዋሎችን በማዘጋጀት ስልጠና ሊሰጥና ወደ አውትግሮወሮች መውረዱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

75. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት አመራረትና ምርት አያያዝ የስልጠና ማንዋሎች የተዘጋጁ ቢሆንም ተግባራዊ እንዲሆኑ የስልጠናና የግንዛቤ ስራዎች በስፋት ባለመከናወናቸው በአርባ ምንጭና በድሬዳዋ የልማት ኮሪዶር የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት አሰባሰብና አያያዝ በአውትግሮዎሩም ሆነ በባለሀብቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ሳይንሳዊ ሂደትን የተከተለ አለመሆኑ ታውቋል፡፡ለምሳሌ ስለ አመራረት ሂደት፣ ድህረ-ምርት አሰባሰብና አያያዝ፣ የምርት ማጠራቀሚያ፣ የምርት አስተሸሸግ፣ የምርት ማጓጓዝ ዘዴ፣ የኬሚካል አጠቃቀምና አያያዝ ባህላዊና ኃላቀር በመሆኑ እና የግንዛቤ እጥረት መኖሩ፣ በመድኃኒት ርጭት ወቅት የሚደረግ የግል ደህንነት (personal safetey) የማያደርጉ መሆኑ እንዲሁም ኤጀንሲው በበሽታና ተባይ መካላከል በወረርሽኝ መልክ ካልተከሰተ በስተቀር ለቅድመ ጥንቃቄ የሚረዳ ሙያዊ እገዛ የማይደረግ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

76. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ኤጀንሲው የሚጠቀምበት የስልጠና ማንዋል መኖሩን ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት አሻሽሎ ለማዘጋጀት ታስቦ አማካሪ ባለሙያ ለመቅጠር በሂደት ላይ መሆኑ፣ ኤጀንሲው ድጋፍና ክትትል የሚያደረገው ወደ ውጭ ኤክስፓርት ለሚያደርጉ ባለሀብቶችና  አውቶግሮዎሮች(የኮንትራት አርሶ አደሮች) ሲሆን ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርቡ አርሶ አደሮችን የመደገፍና ስልጠና የመስጠት ኃላፊነት የግብርና ሚኒስቴር መሆኑን፣ በመቂ አካባቢ ያሉ አውትግሮዎሮች በአካባቢው ኤክስፖርት የሚያደርግ ካምፓኒ ጋር በውል በማስተሳሰር ማህበሩ(ዩኒየኑ) ባሉት የማቀነባበሪያ፣ ማዘጋጃና የማቀዝቀዣ ክፍሎች በመጠቀም በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ምርታቸውን በማምረት እና ለካምፓኒው በማስረከብ ካምፓኒው ካመረተው ምርት ጋር ኤክስፖርት የሚደረግበት አሰራር እንዲኖር በማድረግ ድጋፍና ክትትል ያደረገ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

77. እንዲሁም በአርባ ምንጭ የሚገኙ አውትግሮዎሮችን የሙዝ ኤክስፖርት  በመቆሙ ምክንያት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ የቆመ መሆኑ፣ በድሬደዋ አስተዳደር ኤክስፖርት የሚያደርጉ ካምፓኒዎች ባለመኖራቸው ኤጀንሲው የኮንትራት አርሶአደር (አውትግሮወር) በማደራጀት ጥራቱን የጠበቀ ምርት ኤክስፖርት እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ያልተቻለ መሆኑ ገልፀዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ በበሽታና ተባይ መከላከል ላይ በግብርና ሚኒስቴር ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገቡ ግብዓቶች ጋር ኳረንታይን የሆኑ ተባይና በሽታ የሚቆጣጠር ክፍል መኖሩን፣ በቲማቲም ሰብል ላይ ተከስቶ በነበረው ተባይ (ቱታ አብሶሉታ) ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ሀገር አቀፍ አውደ ጥናት በማዘጋጀት የኬሚካል ሙከራ ተሰርቶ ችግሩን ለመፍታት የተቻለ መሆኑን፣ የግል ደህንነት (personal safetey) በተመለከተ በአበባው የልማት

መስክ በተዘጋጀው የመልካም አመራረት ስርዓት(Code of Practice) ተሞክሮን በአትክልትና ፍራፍሬ ላይ በማዘጋጀት በአቅርቦትና በአጠቃቀም ላይ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

78. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በስፋት የሚከናወንባቸው አካባቢዎችን በመለየት አርሶ አደሮችን በማደራጀት በአውትግሮዎር ደረጃ አቅም በመፍጠር ጥራቱን የጠበቀ ምርት እንዲያመርቱ በማድረግ ኤክስፖርት እንዲያደርጉ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

79. የሆርቲካልቸር ኤጀንሲው ዘርፉን የሚደግፍ ቴክኖሎጂዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር በመሰብሰብ፣ ልማቱ ላይ የመሰኖ አጠቃቀም፣ የአግሮኖሚ እንክብካቤ፣ ዝሪያ አመራረጥ፣ ምርት አጠባበቅና፣ ሌሎች የአትክልትና ፍራፍሬ ቴክኖሎጂ ፓኬጅ ያካተተ የሙያ ማሻሻያ አውደጥናትና ስልጠና እንዲሁም የአቅም ግንባታ ድጋፎች በተጠናከረ መልኩ መስጠት ካልተቻለ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት አሰባሰብ እና አያያዝ ሳይንሳዊ ሂደትን የተከተለ እንዳይሆን፣ ከፍተኛ የሆነ የምርት መጠንና ጥራት እንዲቀንስና በግብይት ወቅት ከፍተኛ የሆነ የምርት ብልሽትና ብክነት እንዲከሰት እና የውጪ ንግድና የምርት ተፈላጊነት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

## ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች አለም አቀፍ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችንና ስታንዳርዶችን ያሟሉ መሆናቸውን በተመለከተ፤

80. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ኤክስፖርት የሚያደርጓቸው ምርቶች አለም አቀፍ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችን እና ስታንዳርዶችን ( የዩሮ ጋፕ፣ ግሎባል ጋፕ፣ አውሮፓ ጋፕ) መሰረት የሚመረቱ መሆኑን ክትትል ሊያደርግ እና በዚህ ረገድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

81. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ኤክስፖርት የሚያደርጉዋቸው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች የምግብ ደህንነት መስፈርቶችና አለማአቀፋዊ ስታንዳርዶች (ኤምፒኤስ፣ቴስኮ፣ የአውሮፓ ጋፕና ግሎባል ጋፕ) የመሳሰሉትን ቤንች ማርኮች በኤጀንሲው በኩል ለባለሀብቶችም ሆነ ለአውትግሮዎሮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ያለመሰራታቸውን፣ በተጨማሪም ለገበያው የሚቀርቡ የሆርቲካልቸር ምርቶች ከደንበኛው ፍላጎት አንፃር እንዲሁም ከየሀገሩ መመሪያ በተጣጣመ መልኩ የገበያውን መስፍርት/ ስታንዳርዶች የማያሟሉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ባለሃብቶችና አውትግሮወሮች እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

82. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችና አለማአቀፋዊ ስታንዳርዶች(ግሎባል ጋፕ፣...) በተመለከተ በኬንያ ወይም በደቡብ አፍሪካ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችና አለማአቀፋዊ ስታንዳርዶችን የኤጀንሲው ባለሞያዎችን ለማሰልጠን ተሞክሮ በበጀት እጥረት ምክንያት ባለመሳካቱ በኤጀንሲው የዕውቀት

ክፍተት በመኖሩ ለኩባንያዎችና አውትግሮወሮች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ያልተቻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን አብዛኞቹ ኤክስፖርት የሚያደርጉ ኩባንያዎች የምግብ ደህንነት መስፈርቶችን ያሚሉ ለመሆናቸው እውቅና እና ሰርተፍኬት ያላቸው መሆኑ ኤጀንሲው የተሻለ አፈፃፀም ካላቸው ሰርቲፋይድ ከሆኑ ባለሀብቶች ተሞክሮ በመውሰድና በመቀመር ወደ ሌሎች የማስተላለፍ ስራ እየተሰራ ያለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

83. ይሁን እንጂ የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ በአለም አቀፍ የምግብ ደህንነት ስታንዳርድ መሰረት ምርቶችን አምርተው ኤክስፖርት እንዲደረግ ለባለሀብቶችም ሆነ ለአውትግሮዎሮች እንዲያውቁት ድጋፍ መስጠት ያልቻሉት በጀት እጥረት መሆኑን ቢገልፁም ለዚህ ጉዳይ የሚውል በጀት ከሚመለከተው አካል ጠይቀው የተከለከሉ መሆናቸውን ወይም በዕቅድ አካተው በበጀት እጥረት ማከናወን አለመቻላቸውን የሚገልፅ ማስረጃ ባለማቅረባቸው የሰጡትን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

84. የሆርቲካልቸል ልማት ኤጀንሲው በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች አለም አቀፍ መስፈርቶችን እና ስታንዳርዶችን መሰረት አድርገው በማምረት ኤክስፖርት እንዲያደርጉ የድጋፍና ክትትል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ካልቻለ በዘርፉ የሚመረተው ምርት በጥራትና በብዛት ተወዳዳሪ ሆኖ በአለም አቀፍ ገበያ መቅረብ እንዳይችል አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የምርት ግብዓት በወቅቱና በሚፈለገው መጠን እንዲቀርብ ድጋፍና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤

85. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በግብዓት አቅራቢነት የተሰማሩ ኩባንያዎች ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በወቅቱ በሚፈለገው ጥራት፣ መጠንና አይነት እንዲቀርቡ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንዲሁም እጥረት በሚፈጠርበት ወቅት በማስተባበር ችግሩን የሚፈታበት አሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

86. ለአትክልትና ፍራፍሬ ግብዓት አቅራቢ የሆነው የግብርና ግብዓት አቅራቢ ድርጅት(AISE) በዘርፉ የሚፈለገውን የምርት ግብዓት በሚፈለገው መጠን፣ አይነትና ወቅት የማቅረብ ችግር ያለበት መሆኑ፣ በተጨማሪም ኬሚካሎችን እና ግሪንሀውስ ፕላስቲክ የምርት ግብዓቶች የማያስመጣ መሆኑ እንዲሁም የግብዓት አቅራቢ አስመጪዎች በቁጥር አነስተኛ በመሆናቸው እጥረት በተከሰተ ቁጥር እርስ በእርስ በመነጋገር ዋጋ የሚሰቅሉ መሆኑ እና ኤጀንሲው የግብዓት አቅርቦት ችግሮችን ለመቅረፍ የአገር ውስጥ አቅራቢዎችንና የሚመለከታቸውን በማስተባበር ድጋፍ ያለመስጠቱን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

87. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የኩባንያዎችን የግብዓት ፍላጎት በየዓመቱ በመሰብሰብ ለግብርና ግብዓት አቅራቢ ድርጅት (AISE) የሚያቀርቡ እና በአትክልትና ፍራፍሬ ዙሪያ የግብዓት እጥረት ችግር ያለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

88. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ለልማቱ የሚያስፈልገውን የግብዓት ፍላጎትና መጠን በመንግስት የግብዓት አቅራቢ ድርጅትም ሆነ በዘርፉ በተሰማሩ የግል የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች እንዲቀርብ የማስተባበር ስራ በተጠናከረ መልኩ መከናወን ካልቻለ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች እና አውትግሮወሮች ለማምረት የሚያስፈልጋቸውን መሰረታዊ ግብዓቶች ሟሟላት ያልቻሉ በመሆኑ ከዘርፉ የሚጠበቀው ምርት በብዛት፣ በዓይነትና በጥራት ወደገበያ እንዲቀርብ ካለማስቻሉም በላይ ለባለሀብቱና ለአገሪቱ እድገት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ አማራጭ ገበያዎችን እንዳይኖሩ በማድረግ ኢኮኖሚያዊ ዋጋ እንዲታጣ ያደርጋል፡፡

## በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች ዕቅድ እና አፈፃፀም ክትትል የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ፤

89. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የዕቅድና የአፈፃፀም ክትትል የሚያደርግ መሆኑ እና በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችን የሚገጥማቸውን ችግሮች በመዳሰስ አፋጣኝ ምላሽ በወቅቱ እንዲያገኙ የሚደረግ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

90. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በዘርፉ የተሰማሩ በየወሩ በመስክ ጉብኝት በማድረግ የአምራቾችን አፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ የማያደርግ መሆኑ እንዲሁም ቋሚና መደበኛ የሆነ የድጋፍና የክትትል ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ እንዲሁም በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ችግሮች ለመለየት የተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች ተደርገው ለሚመለከተው አካል ያልቀረቡ መሆናቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

91. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በእቅዳችን መሰረት ከእያንዳንዱ ኩባንያ ጋር በየወሩ በመስክ ጉብኝት ክትትልና ድጋፍ የማናደርግ ቢሆንም በሰው ኃይል እና በትራንስፖርት ችግር በየ3ወሩ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርጉ መሆኑን፣ በመስክ ጉብኝት ወቅት አብዛኞቹ ካምፓኒዎች የሚያነሱት ችግር የመሰረተ ልማት (የውሃ፣ የመንገድ፣ የመብራትና የስልክ) ችግሮች ያለባቸው መሆኑን እንደሆነና የተነሱትን ችግሮች በመያዝና በመሰብሰብ ችግሮቹ እንዲፈቱ በሚመለከተው ዳይሬክቶሬት በኩል ከባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት የሚደረግ መሆኑን፣ ባለሀብቶች ባላቸው አቅም በሶስት የሚከፈሉ መሆኑን እነሱም ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ተብለው ሲሆን ከፍተኛ የሚባሉት ባለሀብቶች ብዙውን ጊዜ የሙያ ድጋፍ የማይፈልጉ መሆኑን ምክንያቱም ካምፓኒዎቹ የሚቀጥሯቸው ባለሙያዎች(የውጪ ዜጎች) እና ልምድ ያላቸው የሀገር ውስጥ ባለሙያዎች በመሆናቸው ሲሆን የኤጀንሲው

ባለሙያዎች ከፍተኛ አቅም ካላቸው ባለሀብቶች ምርጥ ተመክሮዎችን በመቀመር ለመካከለኛና ዝቅተኛ አቅም ላላቸው ባለሀብቶች እውቀት እና ክህሎት የማስተላለፍ ስራ የሚሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

92. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች አፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በዘርፉ የሚነሱ ችግሮችን በወቅቱ ከሚመለከተታቸው አካላት ጋር በመሆን አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙ የሚደረግበት አሰራር ያልተጠናከረ እና ለዘርፉ ልማት እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን ለመለየት በየጊዜው የደሰሳ ጥናቶች በማካሄድ መፍትሂ የሚወሰድበት ሁኔታ ባለመፈጠሩ በልማቱ ዙሪያ በየጊዜው የሚነሱ ቅሬታዎች ፈጥነው ምላሽ እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡

**ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ጥራቱን የጠበቀ እና ተወዳዳሪ ምርት ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንዲቻል ድጋፍና ክትትል ማድረጋቸውን እንዲሁም ከአልሚ ባለሀብቶች፣ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤**

**የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላኪ ድርጅቶችና ዩኒየኖች የውጪ ንግድ አፈፃፀም መከታተሉን በተመለከተ፤**

93. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላኪ ድርጅቶች የውጪ ንግድ የምርት ሽያጭ የመንግስት ፖሊሲ፣ መመሪያና ደንብን ተከትለው መፈፀማቸውን እንዲሁም ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች በተያዘው እቅድና በተፈጽመው ውል መሰረት መከናወናቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

94. ባለሀብቶች በየአመቱ ኤክስፖርት የሚያደርጉትን የምርት መጠን ዕቅድ ለኤጀንሲው ቢያሳውቁም እቅዳቸው መሰረት አድርገው ለውጭ ገበያ ማቅረብ አለመቻላቸውን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ኩባንያዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

95. እንዲሁም በ2003 እና በ2004 ዓ.ም የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ በዘርፉ የተሰማሩ ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት ለማድረግ በምርት መጠንና በገቢ ያቀደ ሲሆን አፈፃፀሙ በምርት መጠን ከዕቅድ በላይ ጭማሪ ያሳየ ቢሆንም በገቢ ክንውኑ ከዕቅዱ ከ50% በታች መሆኑ፣

- በ2003 ዓ.ም በመጠን ዕቅድ 74.3 ሺ ቶን ኤክስፖርት ለማድረግ ታቅዶ 93.01 ሺ ቶን(125 በመቶ) የተከናወነ ቢሆንም የሽያጭ ገቢ ዕቅድ 153 ሚሊዮን ዶላር ለመሰብሰብ ታቅዶ 40 ሚሊዮን ዶላር (26.1 በመቶ) ብቻ መከናወኑ፣
- በ2004 ዓ.ም በመጠን ዕቅድ 149.9 ሺ ቶን ኤክስፖርት ለማድረግ ታቅዶ 224.77 ሺ ቶን(149.9 በመቶ) የተከናወነ ቢሆንም የሽያጭ ገቢ ዕቅድ 126.04 ሚሊዮን ዶላር ለመሰብሰብ ታቅዶ 53.15 ሚሊዮን ዶላር(42.05 በመቶ) ብቻ የተከናወነ መሆኑ፣

96. በ2005 እና በ2006 ዓ.ም የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ በዘርፉ የተሰማሩ ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት ለማድረግ በምርት መጠንና በገቢ ያቀደ ሲሆን አፈፃፀሙ በምርት መጠንም በገቢ ክንውኑ ከዕቅድ በታች መሆኑ፣

- በ2005 ዓ.ም በመጠን ዕቅድ 148.96 ሺ ቶን ክንውን 137.66 ሺ ቶን(92.40 በመቶ) እና በገቢ ዕቅድ 153.11 ሚሊዮን ዶላር ክንውን 49.63 ሚሊዮን ዶላር(32.41 በመቶ)
- በ2006 ዓ.ም በመጠን ዕቅድ 249.54 ሺ ቶን ክንውን 145.11 ሺ ቶን(58.15 በመቶ) እና በገቢ ዕቅድ 158.73 ሚሊዮን ዶላር ክንውን 45.72 ሚሊዮን ዶላር(28.80 በመቶ) መሆኑ፣

| በጀት ዓመት (2003-2006) | የምርት ዓይነት (Type) | ወደ ውጪ የተላከ(Export) | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በመጠን(በሺ ቶን) | | | | በገቢ(በሚሊዮን ዶላር) | | | |
| | | ዕቅድ | | ክንውን | በመቶኛ | ዕቅድ | | ክንውን | በመቶኛ |
| | | ስትራቴጂክ | ዓመታዊ | | | ስትራቴጂክ | ዓመታዊ | | |
| 2003 | አትክልት (Vegitables) | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | ፍራፍሬ (Fruits) | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | ድምር(Sum) | 73.47 | 74.3 | 93.01 | 125 | 148.0 | 153 | 40 | 26.1 |
| 2004 | አትክልት (Vegitables) | - | 35.8 | 110.67 | 309.1 | - | 51.9 | 48.66 | 93.7 |
| | ፍራፍሬ (Fruits) | - | 114.1 | 12.93 | 11.3 | - | 74.5 | 4.49 | 6.0 |
| | ድምር(Sum) | 338.6 | 149.9 | 224.77 | 149.9 | 313.7 | 126.4 | 53.15 | 42.05 |
| 2005 | አትክልት (Vegitables) | - | 95.91 | 123.57 | - | 128.8 | 123.41 | 48.6 | 39.4 |
| | ፍራፍሬ (Fruits) | - | 53.05 | 14.09 | - | 26.6 | 29.7 | 4.03 | 13.6 |
| | ድምር(Sum) | 517.5 | 148.96 | 137.66 | 92.40 | 155.4 | 153.11 | 49.63 | 32.41 |
| 2006 | አትክልት (Vegitables) | - | 181.27 | 126.46 | - | 69.8 | 137.12 | 39.78 | 29.0 |
| | ፍራፍሬ (Fruits) | - | 68.27 | 18.65 | - | 27.3 | 21.61 | 5.94 | 27.5 |
| | ድምር(Sum) | 741.0 | 249.54 | 145.11 | 58.15 | 97.1 | 158.73 | 45.72 | 28.80 |

97. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላኪ ድርጅቶችና ዩኒየኖች የውጪ ንግድ የምርት ሽያጭ ሲያከናውኑ የመንግስት ፖሊሲ፣ መመሪያና ደንብን ተከትለው መፈፀማቸውን ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ ስልጣን ኤጀንሲው የሌለው መሆኑን ነገር ግን የኤክስፖርት ሂደቱ የተሳለጠ እንዲሆን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የዘርፉ ደንብና መመሪያ እንዲተገበሩ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን፣ በሙዝ ተቀባይና ላኪ ኩባንያ መካከል የስምምነት ሰነድ እንዲፈራረሙ የተደረገ መሆኑን ነገር ግን በተቀባይ ኩባንያው መዘግየት ምክንያት እስካሁን ወደ ተግባር ያልተገባ መሆኑን እና በአትክልትና ፍራፍሬ ላይ የገበያውን ፍላጎት በማሟላት የንግድ ትስስር የፈጠሩ ባለሀብቶች ጥቂት በመሆናቸው የተሰራ ስራ አጥጋቢ ያለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

98. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ በነባራዊ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ለዕቅድ ክንውኑ ማነስ በዋናነት የሚጠቀሰው ሰፊ መሬት ተሰጥቷቸው ያላለሙ ባለሀብቶች መኖራቸው፣ በተለይ ለአጎራባች ሀገሮች የሚላከው የአትክልተና ፍራፍሬ ምርት በመጠን ከፍተኛ ቢሆንም በዋጋ ረገድ ከጥራትና ከሀገሮቹ ስምምነት ጋር በተያያዘ ዝቅተኛ ዋጋ የሚከፈልበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡
99. ኤክስፖርት ለማድረግ ወደዘርፉ የገቡ ኩባንያዎች በዕቅዳቸው መሰረት ምርታቸውን በብዛትና በጥራት ኤክስፖርት ማድረግ ካልቻሉ በዘርፉ ሊገኝ የታቀደው የውጭ ምንዛሬ እንዲታጣ ያደርጋል፡፡

## የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎች ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤

100. የሆርቲካልቸር ምርት ልማት ኤጀንሲ የምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎች በተፈፀመው ውል መሰረት ደረጃቸውን የጠበቁና በወቅቱ የተዘጋጁ መሆናቸውን የሚከታተልበት የሚቆጣጠርበት እና ድጋፍ የሚያደርግበት ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
101. ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ኤክስፖርት አገልግሎት የሚውሉ አገራዊ የፓኬጂንግ ስታንዳርድ (specification and standard) የሌለ መሆኑ እና ኤክስፖርቱ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ማምረት የሚችሉ ሀገራዊ ፋብረካዎች ያልተጠናከሩ መሆናቸው እንዲሁም ወደ ጅቡቲ የሚላከው የአትክልትና ፍራፍሬ አላላክና አስተሻሸግ ጥራት የጎደለው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች ለመረዳት ተችላል፡፡

102. ስለጉዳዩ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ኤክስፖርት ለማድረግ በሀገር ደረጃ የተዘጋጀ ስታንዳርድ ባለመኖሩ ኩባንያዎች የተቀባይ ኩባንያዎችን ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ ከውጪ ሀገር እያስመጡና በሀገር ውስጥም እንዲዘጋጅላቸው እያደረጉ ምርታቸውን በመላክ ላይ እንደሚገኙ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት ላይ ከደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር የምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎች መስፈርት (ስታንዳርድ) እንዲወጣላቸው እየሰሩ መሆኑ እንዲሁም ችግሮቹን ለመፍታት ባለድርሻ አካላት የካርቶን አምራች ፋብሪካዎችን ሙሉ ትብብርና ፍላጎት የሚጠይቅ በመሆኑ የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት ቀጣይ ጥረቶችን ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

103. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት የሚያገለግሉ የምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎች ደረጃ በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ የአትክልትና ፍራፍሬ ማሸጊያ ደረጃውን ጠብቆ እንዳይመረት፣ ባለሀብቶች ከውጪ በማስገባት ለከፍተኛ ወጪ ሊዳርጋቸው እና ከውጪ እስኪመጣ ያቅርቦት መዘግየትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

**የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዣ፣ የትራንስፓርትና ሌሎችም የሎጂስቲክስ ፍላጎቶችን እንዲሟሉላቸው ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ፤**

104. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዣ፣ የትራንስፓርትና ሌሎችም የሎጂስቲክስ ፍላጎቶች ከሌሎችም ሀገሮችን ልምድ በማጥናት ተግባራዊ እንዲደረግ ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡

105. የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በኢትዮጲያ አየር መንገድን ከፍተኛ የበረራ ፕሮግራም መዛባት(መዘግየት) የተነሳ ባለሀብቶች የሚልኳቸውን ምርቶች በወቅቱ ለደንበኞቻቸው ስለማይደረስ ተጨማሪ ወጪዎች እና የጥራት ጉድለቶች የሚከሰቱ መሆኑና በተለይም ወደ አፍሪካ አገሮች ምርቶችን ለመላክ የአውሮፕላን በቂ ቦታ ባለመኖሩ ምርቶችን በተፈለገው መጠን ለመላክ ያልተቻለ መሆኑ በኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

106. እንዲሁም በአርባ ምንጭ የምርት ማደራጃና ማቀዝቀዣ መጋዘን በኢትዮጲያ ባህር ትራንስፖርት ሎጂስቲክ አገልግሎት ድርጅት ግንባታው እንዲከናወን በ2005 ዓ.ም ስምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም እስካሁን ግንባታው ያልተጀመረ መሆኑ እና የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በብዛት የሚመረትባቸው አካባቢዎች (አርባ ምንጭ፣ ራያቆቦ፣ ምሰራቅ ሀረርጌና ድሬደዋ) የተሟላ የምርት ማደራጂያና ማከማቻ መጋዘን ያለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

107. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የሴክተሩ እንቅስቃሴ አዲስ እንደመሆኑ መጠን ኤጀንሲው ሲቋቋም የነበሩ የበላይ አመራሮች በኬኒያና በሆላንድ በመገኘት የተሻለ ተሞክሮዎችን በመቀመር ወደ ተግባር ለመተርጎም የተቻለ መሆኑንና በአዲስ አበባ ካርጎ ተርሚናል፣ በባህር ዳርና በመቀሌ ኤርፖርት የማቀዝቀዣ ፋሲሊቲዎች እንዲሟሉ የተደረገ መሆኑን፣ የአዲስ አበባ ካርጎ ተርሚናል ብቃት ያለው አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ መሆኑን፣ በረራና የኩልቼይን አፈፃፀምን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በተዘጋጁ ቅፆች መሰረት መረጃዎች በየጊዜው እየተሰበሰቡ ሪፖርቶች ተጠናቅረው የማስተካከያ እርምጃዎች በየጊዜው የሚወሰዱ መሆኑን፣ አምራች ኩባንያዎች በቂ የሆነ ምርት ባለማምረት ምክንያት ወደ ውጪ የሚላከው ምርት ካርጎው ካልሞላ ሊሄድ የማይችል መሆኑን ገልፀው ችግሮቹን ለመፍታት ከአየር መንገድ ጋር በጋራ የሚሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

108. በመቀጠልም የአርባምንጭ የሙዝ ኤክስፖርት ባለመጀመሩና በገኘና በሻጭ መካከል ያለው የንግድ ትስስር ባለመጠናከሩ ግንባታውን እንዲካሄድ ሥልጣን የተሰጠው የባሕርና ሎጂስቲክ አገልግሎት ድርጅት በቅድሚያ አዋጭነቱን ማየት ስለመረጠ ያልተከናወነ መሆኑ፣ ራያ ቆቦ የምርት ማደራጃና ማከማቺያ በመቀሌ በዩኒ ፍሩት ባለሀብት የተሰራ መሆኑ፣ በድሬደዋ የምርት

ማደራጃና ማከማቺያ በእርዳታ የተገነባ ቢሆንም የውስጥ ግብአቶች ያልተሟሉ መሆኑን፣ በቀጣይ ከኤክስፖርት እድገት ጋር የተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ክትትል የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

109.የሆርቲካልቸር ምርት ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከመንጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዣ፣ የትራንስፖርትና ሌሎችም የሎጂስቲክስ ፍላጎቶች የሚሟሉበትን ሁኔታ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እንዲሟላ ጥረት ካልተደረገ ምርቱ በጥራትና በብዛት ለውጪ ገበያ እንዳይቀርብና ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ተጠቃሚ መሆናቸውን በተመለከተ፤

110. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የገበያ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ሊያሰራጭ እና በአምራቾች መካከል የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

111. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብና ለተጠቃሚዎች ከማድረስ አንፃር የተሰራ ስራ ያለመኖሩ እና ዋና ዋና ገበያዎችን በማየት ባለሀብቶችን ለመደገፍ የሚያስችል የገበያ መረጃ ስርዓት ያልዘረጋና የገበያ ትስስር ያልተፈጠረ በመሆኑ አምራቾች የገበያ መረጃ የማጣት ችግር ያጋጠማቸው መሆኑ በኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ታውቋል፡፡

112.እንዲሁም በኤጀንሲው ፍራፍሬን በተለይ የሙዝ ምርትን በተመለከተ የሳውዲ አረቢያ የገበያ ዋጋ፣ የጥራት መረጃ እና የማሸጊያ ፍላጎት የመሳሰሉት መረጃዎች ተሰብስበው እና ከሙዝ አምራቾች ዩኒየንና ኮሜርሺያል የሙዝ አምራቾች ጋር በጋራ በመሆን የሙዝ አቅርቦት ዝርዝር መረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም በሌሎቹ የአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ የገዢዎችን ሀገራት የጥራት ፍላጎት ደረጃዎችን ለይቶ መረጃዎችን በማጠናቀር ለአምራች ላኪዎች እንዲሰራጭ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ቃለመጠይቅ በቀረበበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

113. በተጨማሪም ወደ ጅቡቲ ኤክስፖርት የሚደረግበት የአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋ ከአለፉት 32 ዓመታት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በአንድ አይነት የመሸጫ ዋጋ እየተሸጠ የሚገኝ መሆኑ፣ ከጅቡቲ ሌላ ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት አማራጭ ገበያ የሌለ መሆኑ በተጨማሪም በድሬደዋ እና በአርባ ምንጭ ያለው የአትክልትና ፍራፍሬ የገበያ ዋጋ ሁኔታ በአካባቢው ያሉ ደላሎች የገበያ ዋጋን እንደፈለጉ የሚጨምሩና የሚቀንሱ በመሆናቸው አምራቹን፣ አርሶ አደሩን ወይም ባለሀብቱን ተጠቃሚ የማያደርግ መሆኑ፣ በአጠቃላይ የተጠኑ የገበያ መዳረሻዎች እና የተዘረጋ የግብይት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ታውቋል፡፡

114.ስለጉዳዩ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በገበያ ዙሪያ ያሉ መረጃዎችን በማሰባሰብና ከተወዳዳሪ ሀገሮች ልምድ በመቅሰም በኬንያና በሆላንድ የስራ ጉብኝቶች ተደርገው ገበያውን ማሻሻል ስለሚቻልበት ሁኔታ የውሳኔ ሀሳቦች ተዘጋጅተው ለግብርና ሚኒስቴር እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲቀርብ ተደርጎ ክትትል በመደረግ ላይ እንደሚገኝ መሆኑ፣ የገበያ ማጣት ችግርን በተመለከተ ከሙዝና ከማንጎ በስተቀር  የገበያ ችግር አለብኝ ብሎ የመጣ የአትክልትና ፍራፍሬ አምራች ባለሀብት ያለመኖሩን እንዲሁም በሙዝና በማንጎ ላይ የገበያ ትስስር ለመፍጠር ሙከራ የተደረገ ቢሆንም በዋጋ ያለመስማማት ትስስሩ ሊካሄድ ያልቻለ ቢሆንም አሁንም ተከታታይ ጥረት እየተደረገ መሆኑን እና የገዢ አካላት የጥራት ፍላጎት ለማወቅ በኤጀንሲው በኩል እየተሰራ መሆኑን ነገር ግን ኤጀንሲው ከዚህ በተሻለ መልኩ ለወደፊት መስራት ያለበት መሆኑ ገልፀዋል፡፡

115. በመቀጠልም በጃፓን፣ በአሜሪካና በሩሲያ የገበያ መዳረሻዎች ጥናት የተካሄደ መሆኑን፣ በአርባ ምንጭ ያሉ ደላሎችን በተመለከተ ከክልሉ ቢሮ ጋር የምክክር ስብሰባ የተደረገ መሆኑንና ክልሉ የደላሎችን ጣልቃ ገብነት የመከላከያ ስልት አዘጋጅቶ እንዲሰራ የተደረገ መሆኑን፣ በጅቡቲ ለሰላሳ ሁለት አመታት ተመሳሳይ የገበያ ዋጋን በተመለከተ ኤጀንሲው የገበያውን ሁኔታ በተመለከተ የዳሰሳ ጥናት በንግድ ሚኒስቴር እንዲጠና መደረጉን ሆኖም ግን የጅቡቲ የገበያ ዋጋ ሁኔታ የፖሊሲ ውሳኔና የሁለቱ ሀገሮች ስምምነትን የማደስ ስራ የሚጠይቅ እንደመሆኑ በበላይ አካላት የሚፈታ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

116. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ኃላፊዎች ክልሉ የደላሎችን ጣልቃ ገብነት የመከላከያ ስልት አዘጋጅቶ እንዲሰራ የተደረገ መሆኑን ቢገልፁም ችግሩ ግን እስካሁን ያልተፈታ መሆኑ ታውቋል፡፡

117. በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀት ለአምራቾች በማሰራጨት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ባለመደረጉ የገበያ መዳረሻዎች እንዳይስፋፉ፣ የገበያ ትስስር እንዳይፈጠር እና ባለሀብቶች ምርታቸውን ኤክስፖርት ማድረግ እንዳይችሉ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## የሀገሪቱን የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

118.በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዱ የመረጃ መረብ በመፍጠር የዚህ መረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊደረግ ይገባል፡፡በኢንቨስትመንት ረገድ የሚወጡ አዳዲስ ወቅታዊ መመሪያዎችን ባለሀብቶች በወቅቱ እንዲያውቁ ሊደረግ ይገባል፡፡

119. በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዳ የመረጃ መረብ (Web Site) ያልተዘረጋ መሆኑ፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በየጊዜው የሚቀያየሩ ቢሆንም ኤጀንሲው በወቅቱ የማስተዋወቅ ስራ የማይሰራ

በመሆኑ እና ለባለሀብቶች በወቅቱ ሳይገለፅ በመቅረቱ አገልግሎት ለማግኘት ወደ መ/ቤቱ(በተለይ ጉምሩክ ላይ) ሲሄዱ ተቀይሯል በማለት የሚጉላሉ መሆኑ በኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች ታውቋል፡፡

120. ስለጉዳዩ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት መልስ የመረጃ መረብ (Web Site) ከዚህ ቀደም ያልነበረና በአሁን ሰዓት ግን በዝርጋታ ላይ የሚገኝ መሆኑ፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በየጊዜው የሚቀያየሩ ቢሆንም ኤጀንሲው በወቅቱ እንዲያውቁት ከማድረግ አንፃር ክፍተቱ ያለ መሆኑን ነገር ግን ባለሀብቶቹ አገልግሎት የሚያገኙባቸውን መ/ቤቶች የመረጃ መረብ (Web Site) መጠቀም የሚችሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

121. በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ያለው የመረጃ ስርዓት ያልተጠናከረ በመሆኑ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች የመረጃ ልውውጡና ስርጭቱ ላይ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እና መረጃ በቀላሉ እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡

## ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ዘርፉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፤

122.በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲና ዘርፉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር ለመፍጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ኤጀንሲው የሆርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለሙያዎች የሚሳተፉበት ቋሚ እና መደበኛ መድረክ በማመቻቸት በጋራ ለልማቱ የሚያግዙ እርምጃዎች የሚወስድበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

123. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በመሬት አሰጣጥ፣ በመሰረተ ልማት ማሟላት፣ በግብዓት አቅርቦት ዙሪያ በአጠቃላይ ዘርፉ የሚጠይቀውን አገልግሎት ከማቀላጠፍና ከማሳደግ ረገድ ያለው ቅንጀታዊ አሰራር የተጠናከረ ያለመሆኑ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ለመስራት በእቅድ የማይመራ መሆኑና ከኦሮሚያ ክልል ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ከሌሎች ክልሎች የተሻለ ቢሆንም መደበኛ የሆነ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑ፣ እንዲሁም የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ፣ የሆርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ቋሚ እና መደበኛ መድረክ ያለ ቢሆንም በታቀደው ጊዜ እየተካሄደ ያለመሆኑ በኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ታውቋል፡፡

124. ስለጉዳዩ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከባለድርሻ አካላትጋር ቅንጅታዊ አሰራር እና የሆርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ቋሚ እና መደበኛ መድረክ ያለ ቢሆንም ወቅቱን ጠብቆ የማይከናወን መሆኑንና ከባለሀብቶች የሚነሱ ችግሮች በወቅቱ የማይፈቱበት ሁኔታዎች መኖሩን ገልፀዋል፡፡

125.የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ከሚመለከታቸው የፌደራል መ/ቤቶች፣ ክልሎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዙሪያ በቅንጅት የሚሰራበት አሰራር ቢኖርም ያልተጠናከረ በመሆኑ እና የሆርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ቋሚ እና መደበኛ መድረክ በታቀደለት የጊዜ ሰሌዳ የማይከናወን መሆኑ በልማቱ ዙሪያ ያሉ ጠንካራና ጎኖች የሚበረታቱበት፣ መልካም ተሞክሮዎች የሚለዋወጡበት እና ባለሀብቶች የሚያነሱዋቸውን ችግሮች በመነጋገር እንዲፈቱ የሚደረግበትን አሰራር እንዳይጠናከር ያደርጋል፡፡

## የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤትን በተመለከተ፤

126.የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች ሊሰበሰቡ፣ ሊደራጁና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ በምርምር ማእከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

127. የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች፣ በምርምር ማእከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ከማድረግ አንፃር የተሰሩ ስራዎች ስለመኖራቸው በኦዲቱ ወቅት መረጃ አልቀረበም፡፡

128. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረቡ ቃለመጠይቆች በሰጡት መልስ የአትክልትና ፍራፍሬ ባለሀብቶች የሚፈልጉት ቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች ያለመኖራቸው እና በሙዝ ላይ ብቻ መኖሩንና እሱንም ለማጠናከር በጋራ እየሰሩ የሚገኙ መሆኑን በተጨማሪም ለኤክስፖርት ግብዓት ትኩረት ያደረጉ የምርምር ማዕከላት መስፋፋት ያለባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡የኤጀንሲው ኃላፊ ይህን ቢሉም በሁሉም የአትክልትና ፍራፍሬ ዙሪያ እንዲሰሩ ቲሹካልቸሮች ሊጠናከሩ ይገባል፡፡

129. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በሁሉም የአትክክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ የሚሰሩ ቲሹካልቸሮች ባለመኖራቸው የተሸሉ የዝርያ ዓይነቶች በመፍጠርና በማባዛት ምርትና ምርታማነት እንዳይጨምር አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

## የስትራቴጂክ እና ዓመታዊ ዕቅድ እና የዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ፤

130. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ  የስራቴጂክ እቅዱን መሰረተ በማድረግ አመታዊ እቅድ ሊያቅድና አፈፃፀሙ ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች መንስኤዎቻቸውን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በእቅድ ዝግጅት ወቅት ነባራዊ ሁኔታን በትክክል ባገናዘበ መልኩ ሊያቅድ፣ የእቅድ ዝግጅቱን ዋና ፈፃሚውንና ባለሀብቱን አሳታፊ ሊያደርግ  እና መድረክ በመፍጠር ሁሉንም ሰራተኞችና ባለሀብቶች እቅድ ላይ በቂ ግንዛቤ(ኦረንቴሽን) ሊሰጥ ይገባል፡፡

131. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ከ2003-2007 ዓ.ም የስትራቴጂክ ዕቅድ ያዘጋጀ ቢሆንም ከ2003 እስከ 2006 ዓ.ም የተዘጋጀው ዕቅድ የስራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ አለመሆኑ(ሰንጠረዥ 3)፣ የ2003-2006 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀም በተለይ በውጪ ንግድ በምርት መጠንም ሆነ በገቢ ከዕቅድ በታች መሆኑ፣ በአፈፃፀም ሪፖርት ላይ በየዓመቱ ተደጋጋሚ ችግሮች የሚገለፁ እና እነዚህን ችግሮች በየበጀት ዓመቱ መንስኤዎቻቸውን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ የማይወሰድባቸው መሆኑ እንዲሁም በእቅድ ዝግጅት ወቅት በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችንና የሚመለከታቸው አካላትን አሳታፊ ያደረገ ያለመሆኑ በኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች ታውቋል፡፡

| በጀት ዓመት | ለአትክልትና ፍራፍሬ ባለሀብቶች ይተላለፋል ተብሎ የታቀደ መሬት በሄክታር እና አፈፃፀሙ | | | የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት የኤክስፖርት ዕቅድ እና አፈፃፀም | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በመጠን(በሺ ቶን) | | | በገቢ(በሚሊዮን ዶላር) | | |
| | በስትራቴጂክ | ዓመታዊ | ክንውን | በስትራቴጂክ ዕቅድ | ዓመታዊ ዕቅድ | ክንውን | በስትራቴጂ ክዕቅድ | ዓመታዊ ዕቅድ | ክንውን |
| 2003 | 5164.7 | | | 73.47 | 74.3 | 93.01 (125%) | 148.0 | 153 | 40 (26%) |
| 2004 | 10513.4 | | | 338.6 | 47.6 | 224.77 (150%) | 313.7 | 126.04 | 53.15 (42%) |
| 2005 | 16080.8 | | | 517.5 | 148.96 | 137.66 (92%) | 155.4 | 153.11 | 49.63 (32%) |
| 2006 | 23040.4 | | | 741.0 | 249.54 | 145.11 (58%) | 97.1 | 158.73 | 45.72 (29%) |

*ሰንጠረዥ 3፡- ከ2003-2006 በጀት ዓመት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም*

132. ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት የነበሩ አቅም ኖሯቸው በኤክስፖርቱ መሬት ተመድቦላቸው ወደ ስራ በመግባት ላይ የነበሩ ኩባንያዎች በተለያየ ምክንያት ከኤክስፖርት ልማቱ በመውጣታቸው እንዲሁም ዓመታዊ ዕቅዶቹ በየበጀት ዓመቱ ባሉት ኩባንያዎችና በሚኖረው ወቅታዊ አፈፃፀም አቅምን በማገናዘብ የሚታቀድ በመሆኑ ልዩነቶቹ የተከሰቱ መሆኑ፣ በእቅድ ዝግጅት ወቅት በዘርፉ ተሰማሩ ባለሀብቶችና የሚመለከታቸው አካላትን አሳታፊ ለማድረግ ከመረጃ አሰባሰብ ጀምሮ እስከ መፅደቅ ሂደጹ ባለድርሻ አካላትን በተለይም አምራች ኩባንያዎችን ለማሳተፍ ጥረት የሚደረግ መሆኑ፣ በወቅታዊ ሪፖርቶች ችግሮች የሚገለፁ እና እነዚህን ችግሮች ለመፍታት በየጊዜውና በየደረጃው ከባለድርሻ አካላት ጋር ጥረት እየተደረገ ቢሆንም በተለይ ከመሰረተ ልማት ጋር የተያያዙት ከሀገር የአቅም ዕድገት ጋር የተያያዙ በመሆኑ በሂደት ዕልባት እያገኙ የሚሄዱ መሆናቸው፣ በሌላ በኩል በተለያዩ ልማት ኮሪደሮች በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ለመሰማራትና ለማስፋፋት

ለሚፈልጉ ባለሀብቶች አመቺ የሆነ የሚለማ መሬት ማቅረብ ያለመቻል ዋና ዋና ምክንያቶች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

133. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት በማድረግ ዓመታዊ ዕቅዶችን የማይዘጋጁ መሆኑ፣ የዕቅድ አፈፃፀሙ ከዕቅድ በታች መሆኑ፣ በአፈፃፀም ሪፖርት ላይ የሚነሱ ችግሮች ወቅታዊ ምላሽ የማያገኙ መኖራቸው እና በእቅድ ዝግጅት ወቅት በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችንና የሚመለከታቸው አካላትን አሳታፊ ያደረገ ካልሆነ ዕቅዱ ግቡን እንዳይመታ እና የአፈፃፀም ችግሮች እንዲከሰቱ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## መደምደሚያዎች

### ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በተመለከተ የኢንቨስትመንት ድጋፍ አሰጣጥ፣ የማበረታቻ ስርዓትና በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የተዘረጋው አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

- ✓ በኤጀንሲው ሊዘጋጅ የሚገባው ሁሉን አቀፍ የድጋፍ ማዕቀፍ የአትክልትና ፍራፍሬን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ዋና ዋና የድጋፍ አይነቶችን ማለትም በግብዓት አቅርቦት ድጋፍ፣ ከምርምርና መሰል ተቋማት በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ በተለይ በዘር ፍተሻ ማለማመድና ማባዛትን በተመለከተ፣ በመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ድጋፍን በተመለከተ፣ በብድር አቅርቦት፣ በውጭ ምንዛሪ አቅርቦትና ዝውውር ድጋፍን በተመለከተ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ በተመለከተ፣ የአለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ለማሟላት የሚያግዝ የቴክኒክና የስልጠና ድጋፍን እንዲሁም ለዘርፉ የሚያስፈልጉ መረጃዎች አቅርቦት እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በመጓጓዝ ሂደት ለሚያጋጥማቸው አደጋና ብልሽት ሊኖር ስለሚችል የዋስትና አቅርቦት ድጋፍ የመሳሰሉ የድጋፍ ዓይነቶችን በዝርዝር በመለየት ድጋፍ የሚሰጠውን አካል ኃላፊነት፣ ድጋፉ ሊገኝ የሚችልበትን ጊዜ፣ በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር በመለየት ከአንድ መስኮት አገልግሎት(One window shopping) መሰረተ ሀሳብን የሚያመላክት ሁሉን አቀፍ የማበረታቻ የድጋፍ ማዕቀፍ በኤጀንሲው ያልተዘጋጀና በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶች እንዲውቁት ያልተደረገ መሆኑ ፣
- ✓ በኤጀንሲው ስትራቴጂክ ዕቅድ(ከ2003-2007ዓ.ም) በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ 23,040.4 ሄክታር መሬት በባለሀብቶች ይለማል ተብሎ ዕቅድ ቢያዝም እስከ 2006 በጀት ዓመት መጨረሻዓ.ም መጨረሻ በባለሀብቶች የተያዘው መሬት 16,756.0 ሄክታር ብቻ መሆኑ፣
- ✓ ኤጀንሲው በየክልሉ የሚገኙ ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምቹ የሆኑ መሬቶችን(ማሳዎችን) በመለየት መሰረታዊ መረጃዎችን በማደራጀት ወደ መሬት ቋት እንዲገቡ እና ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ የማስተዋወቅ ስራ ያልተሰራባቸው መሆኑ፣
- ✓ በአትክልትና ፍራፍሬ የተሰማሩ ባለሀበቶች የአዋጭነት ጥናት ሳያቀርቡ ወደ ልማቱ የገቡ ባለሀብቶች መኖራቸውና ያቀረቡትም ቢሆኑ የአዋጭነት የጥናት ሰነዱ ደረጃውን የጠበቀ፣ አዋጭነቱ አሰተማማኝ የሆነና ጥናቱ ሊተገበር የሚችል መሆኑ ተገምግሞ የፀደቀ ስለመሆኑ የሚገልፅ መረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ✓ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች(መብራት፣ ውኃ፣ ስልክ፣ መንገድ፣ …ወዘተ) በወቅቱ የማይሟላላቸው መኖራቸው፣

- ✓ አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የብድር አገልግሎቶች የማያገኙ መኖራቸው፣
- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማቶችን በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ በኤጀንሲው ድጋፍና ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣
- ✓ ለክላስተር የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለለ ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በወቅቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ መሆናቸው እና በኤጀንሲው እርምጃ የማይወሰድባቸው መሆኑ፣
- ✓ የኤክስፖርት አትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎች ለማምረት ውል ቢገቡም ለሀገር ውሰጥ ገበያ የሚያቀርቡና ከውሉ ውጪ ሌሎች ሰብሎችን የሚያመርቱ ባለሀብቶች መኖራቸው፣
- ✓ ባለሀብቶች ኤክስፖርት የሚያደርጉትን ምርት በየዓመቱ በዕቅድ ቢያዝም በዕቅዱ መሰረት ኤክስፖርት የማያደርጉና በኤጀንሲው በኩል ክትትልና ድጋፍ የማይደረግ መሆኑ፣
- ✓ ሞዴል የሆኑ የአትክልትና ፍራፍሬ ኩባንያዎች ቀልጣፋ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን በኤጀንሲው ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣

**ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምርት እና ምርታማነትን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ስርዓት ዘርግቶ በአገር ውስጥ እና በዓለም ዓቀፍ ገበያ ጥራቱን የጠበቀ ተወዳዳሪ ምርት ለማምረት እንዲቻል የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤**

- ✓ በተከታታይ የቴክኖሎጂ ማስረፅ (የሆርቲካልቸር ስራ ዘርፍ በቂ ክህሎትና የስራ ተነሳሽነት በማዳበር ሙያዊ ድጋፍ ከመስጠት አንፃር) የአቅም ግንባታ ድጋፎች በተጠናከረ መልኩ የማይሰጡ መሆናቸው፣
- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትና ምርት አያያዝ የአፈፃፀም ማንዋሎች(የስልጠና ሰነዶች) ቢኖሩም በቂ ስልጠናና ግንዛቤ ያልተከናወነባቸው መሆኑ፣
- ✓ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችና አለማአቀፋዊ ስታንዳርዶች (ኤምፒኤስ፣ቴስኮ፣ የአውሮፓ ጋፕና ግሎባል ጋፕ) የመሳሰሉትን ቤንች ማርኮች በኤጀንሲው በኩል ለባለሀብቶችም ሆነ ለአውትግሮዎሮች እንዲያውቁት ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ የግብርና ግብዓት አቅራቢ ድርጅት(AISE) የመንግስት ድርጅት ሆኖ የሚፈለገውን የምርት ግብዓት በሚፈለገው መጠን፣ አይነትና ጊዜ የማቅረብ ችግር ያለበት መሆኑ እና ኬሚካልና ሌሎች እንደ ግሪንሀውስ ፕላስቲክ የመሳሰሉትን የምርትና የኢንቨስትመንት ግብዓቶች በማስመጣት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣
- ✓ የግብዓት አቅራቢ አስመጪዎች በቁጥር አነስተኛ በመሆናቸው እጥረት በተከሰተ ቁጥር እርስ በእርስ በመነጋገር ዎጋ የሚሰቅሉ መሆኑ፣
- ✓ የማዳበሪያና ኬሚካል አቅርቦት በሚፈለገው አይነት፣ መጠን፣ ወቅት እና ተወዳዳሪ ዎጋ ማቅረብ የሚችሉ ብቁ ድርጅቶች ያለመኖራቸው፣

- ✓ በሆርቲካልቸር ልማት የተሰማሩ አውትግሮዎሮች በቁጥር አነስተኛ መሆናቸው እና አውትግሮዎሮቹና አምራቾቹ በቂና ተከታታይነት ያለው የክህሎት ስልጠናዎች የማያገኙ መሆናቸው፣
- ✓ በኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎችን ለመደገፍና ለመከታተል የሚያስችል ቋሚና መደበኛ የሆነ የድጋፍና የክትትል ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- ✓ በኤጀንሲው በመስክ ጉብኝት በሚደረግበት ወቅት ከባለሀብቶቹ ጋር በችግሮቻቸው ዙሪያ ከመናገር(ከመወያየት) እና ከመፃፍ ያለፈ ወቅታዊ እና አፋጣኝ ምላሽ የማይሰጥ መሆኑ፣

**የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ጥራቱን የጠበቀ እና ተወዳዳሪ ምርት ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንዲቻል ድጋፍና ክትትል ማድረጋቸውን እንዲሁም ከአልሚ ባለሀብቶች፣ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤**

- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት ምርቶች በዎጋና በጥራት ተወዳዳሪነታቸውን ለማረጋገጥ ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ በመነሳት የተሻለ አመራረት፣ ጥራትና የምግብ ደህንነት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲኖር ከሆርቲካልቸር ማህበር ጋር በመተባበር የስልጠና እና የምክር አገልግሎት የሚሰጥበት አሰራር ስለመኖሩ መረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ✓ ኤጀንሲው የገገሮዎችን ሀገራት የጥራት ፍላጎት ደረጃዎችን ለይቶ መረጃዎችን በማጠናቀር ለአምራች ላኪዎች የማያሰራጭ መሆኑ፣
- ✓ የኤክስፖርት አፈፃፀምና ለገበያው የሚቀርቡ የሆርቲካልቸር ምርቶች ከደንበኛው ፍላጎት አንፃር እንዲሁም ከየሀገሩ መመሪያ በተጣጣመ መልኩ በጥራት፣ በአይነትና በመጠን በወቅቱ ተሟልቶ የማይቀርብ መሆኑ (የገበያውን መስፍርት/ ስታንዳርዶች ያለማሟላት)፣
- ✓ በየዓመቱ (ከ2003-2006ዓ.ም) ኤክስፖርት የሚደረገው ምርት በመጠንም ሆነ በገቢ ክንውኑ ከዕቅድ በታች መሆኑ፣
- ✓ ለሆርቲካልቸር ኤክስፖርት የተዘጋጁ አገራዊ የፓኬጂንግ ስታንዳርድ (specification and standard) ያለመኖሩ
- ✓ በኢትዮጲያ አየር መንገድን ከፍተኛ የበረራ ፕሮግራም መዛባት(መዘግየት) የተነሳ ባለሀብቶች የሚልኳቸውን ምርቶች በወቅቱ ለደንበኞቻቸው የማይደርስና ተጨማሪ ወጪዎች እና የጥራት ጉድለቶች የሚከሰቱ በመሆኑ በኤጀንሲው ክትትል በማድረግ ችግሩ እንዲፈታ ጥረት ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በብዛት የሚመረትባቸው አካባቢዎች (አርቦ ምንጭ፣ ራያቆቦ፣ ምሰራቅ ሀረርጌና ድሬደዋ) የተሟላ የምርት ማደራጃና ማከማቻ መጋዘን ያለመኖሩ፣

- ✓ ኤጀንሲው የገበያ መረጃዎችን ከማሰባሰብና ተጠቃሚ ከማድረግ አንፃር የተሰራ ስራ ያለመኖሩ እና ዋና ዋና ገበያዎችን በማየት ባለሀብቶችን ለመደገፍ የሚያስችል የገበያ መረጃ ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ✓ ወደ ጅቡቲ ኤክስፖርት የሚደረገው የአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋ በጅቡቲ ከአለፉት 32 ዓመታት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በአንድ አይነት የመሸጫ ዋጋ እየተሸጠ የሚገኝ መሆኑ፣
- ✓ በኤጀንሲው በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዳ የመረጃ መረብ (Web Site) ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- ✓ ዘርፉን የሚመለከቱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በየጊዜው የሚቀያየሩ(በተለይ በጉምሩክ) ቢሆንም ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን በወቅቱ የማስተዋወቅ ስራ የማይሰራ መሆኑ፣
- ✓ ኤጀንሲው የሆርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ቋሚ እና መደበኛ መድረክ ያለ ቢሆንም በታቀደው ጊዜ እየተካሄደ ያለመሆኑ፣
- ✓ ዘርፉ የሚጠይቀውን አገልግሎት ከማቀላጠፍና ከማሳደግ ረገድ ያለው ቅንጅታዊ አሰራር የተጠናከረ ያለመሆኑ፣
- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች፣ በምርምር ማዕከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ከማድረግ አንፃር የተሰሩ ስራዎች ያለመኖራቸው፣
- ✓ ኤጀንሲው ከ2003-2007 ዓ.ም የስትራቴጂክ ዕቅድ ያዘጋጀ ቢሆንም ከ2003 እስከ 2006 በጀት ዓመት የተዘጋጀው ዕቅድ ግን የስራቴጂክ እቅዱን መሰረተ በማድረግ የተዘጋጀ አለመሆኑ፣
- ✓ ኤጀንሲው በእቅድ ዝግጅት ወቅት በዘርፉ የተሰማሩ ሁሉንም ባለሀብቶችንና የሚመለከታቸው አካላትን አሳታፊ ያደረገ ያለመሆኑ፣

134. በአጠቃላይ በአገሪቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማቱን ለማስፋፋትና ሃገሪቷም(ህብረተሰቡም) ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ኤጀንሲው ከሌሎች የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም ከባለሀብቶች ጋር በመቀናጀትና በማስተባበር በርካታ ሥራ መስራቱ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የአትክልትና ፍራፍሬ ልማቱን ለማሳደግ በመስኩ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ይበልጥ ለማገዝና ለማበረታታት በአቅም ግንባታ፣ በግብይትና ፕሮሞሽን፣ በኢንቨስትመንት ድጋፍ አገልግሎት እና በግብዓት አቅርቦት ዙሪያ ትኩረት በመስጠት ልማቱን ለማከናወን የሚያስችል ስርዓት በአግባቡ ሥራ ላይ ካልዋለ እንዲሁም ተግባራዊነቱ የሚያረጋግጥ ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ካልተዘረጋ የተጀመረው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማቱን ለማስፋፋትና ሀገራችን ከልማቱ ተጠቃሚ እንድትሆን የሚሰራው ሥራ ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ያሻሽላሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

### ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በተመለከተ የኢንቨስትመንት ድጋፍ አሰጣጥ፣ የማበረታቻ ስርዓትና በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የተዘረጋው አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

- ✓ በኤጀንሲው ሊዘጋጅ የሚገባው ሁሉን አቀፍ የድጋፍ ማዕቀፍ የአትክልትና ፍራፍሬን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ዋና ዋና የድጋፍ አይነቶችን ማለትም በግብዓት አቅርቦት ድጋፍ፣ ከምርምርና መሰል ተቋማት በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ በተለይ በዘር ፍተሻ ማለማመድና ማባዛትን በተመለከተ፣ በመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ድጋፍን በተመለከተ፣ በብድር አቅርቦት፣ በውጭ ምንዛሪ አቅርቦትና ዝውውር ድጋፍን በተመለከተ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ በተመለከተ፣ የአለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ለማሟላት የሚያግዝ የቴክኒክና የስልጠና ድጋፍን እንዲሁም ለዘርፉ የሚያስፈልጉ መረጃዎች አቅርቦት እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በመጓጓዝ ሂደት ለሚያጋጥማቸው አደጋና ብልሽት ሊኖር ስለሚችል የዋስትና አቅርቦት ድጋፍ የመሳሰሉ የድጋፍ ዓይነቶችን በዝርዝር በመለየት ድጋፍ የሚሰጠውን አካል ኃላፊነት፣ ድጋፉ ሊገኝ የሚችልበትን ጊዜ፣ በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር በመለየት ከአንድ መስኮት አገልግሎት(One window shopping) መሰረተ ሀሳብን የሚያመላክት ሁሉን አቀፍ የማበረታቻ የድጋፍ ማዕቀፍ ኤጀንሲው ሊያዘጋጅና በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶች እንዲውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ኤጀንሲው በየክልሉ የሚገኙ ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምቹ የሆኑ መሬቶችን(ማሳዎችን) በመለየት መሰረታዊ መረጃዎችን በማደራጀት ወደ መሬት ቋት እንዲገቡ እና ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ የማስተዋወቅ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ✓ በአትክልትና ፍራፍሬ የተሰማሩ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት እንዲያቀርቡና የሚቀርቡ የአዋጭነት ጥናቶች ደረጃውን የጠበቀ፣ አዋጭነቱ አሰተማማኝ የሆነና ጥናቱ ሊተገበር የሚችል መሆኑ ተገምግሞ ሊፀድቅ ይገባል፡፡
- ✓ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች(መብራትመ ውኃ፣ ስልክ፣ መንገድ፣ …ወዘተ) በወቅቱ ሊሟላላቸው ይገባል፡፡
- ✓ አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የብድር አገልግሎቶች የሚያገኙበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማቶችን በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ በኤጀንሲው ድጋፍና ክትትል የሚደረግበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ✓ ኤጀንሲው ለክላስተር የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለለ ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በወቅቱ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በውሉ መሰረት የማይሰሩ ባለሀብቶች ላይ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ✓ ሞዴል የሆኑ የአትክልትና ፍራፍሬ ኩባንያዎች ቀልጣፋ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን በኤጀንሲው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

**ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምርት እና ምርታማነትን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ስርዓት ዘርግቶ በአገር ውስጥ እና በዓለም ዓቀፍ ገበያ ጥራቱን የጠበቀ ተወዳዳሪ ምርት ለማምረት እንዲቻል የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤**

- ✓ በተከታታይ የቴክኖሎጂ ማስረፅ (የሆርቲካልቸር ስራ ዘርፍ በቂ ክህሎትና የስራ ተነሳሽነት በማዳበር ሙያዊ ድጋፍ ከመስጠት አንፃር) የአቅም ግንባታ ድጋፎች በተጠናከረ መልኩ ለባለሀብቱም ሆነ ለአውትግሮዎሩ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትና ምርት አያያዝ የአፈፃፀም ማንዋሎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡
- ✓ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችና አለማአቀፋዊ ስታንዳርዶች (ኤምፒኤስ፣ቴስኮ፣ የአውሮፓ ጋፕና ግሎባል ጋፕ) የመሳሰሉትን ቤንች ማርኮች በኤጀንሲው በኩል ለባለሀብቶችም ሆነ ለአውትግሮዎሮች እንዲያውቁት ሊደረግ ይገባል፡፡
- ✓ ኤጀንሲው በግብዓት አቅራቢነት የተሰማሩ ኩባንያዎች በማጠናከር ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በዓይነትና በመጠን እንዲቀርቡ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግና እጥረት በሚፈጠር ወቅት በማስተባበር ችግሩን የሚፈታበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ኤጀንሲው በሆርቲካልቸር ልማት የሚሰማሩ አውትግሮዎሮች እንዲደራጁ ሊያደርግ እና አውትግሮዎሮቹና አምራቾቹ በቂና ተከታታይነት ያለው የክህሎት ስልጠናዎች እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ በኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎችን ለመደገፍና ለመከታተል የሚያስችል ቋሚና መደበኛ የሆነ የድጋፍና የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና በየጊዜው ከባለሀብቶች የሚነሱ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ የሚያገኙበት አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡

**ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ጥራቱን የጠበቀ እና ተወዳዳሪ ምርት ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንዲቻል ድጋፍና ክትትል ማድረጋቸውን እንዲሁም ከአልሚ ባለሀብቶች፣ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤**

- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት ምርቶች በዎጋና በጥራት ተወዳዳሪነታቸውን ለማረጋገጥ ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ በመነሳት የተሻለ አመራረት፣ ጥራትና የምግብ ደህንነት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲኖር ከሆርቲካልቸር ማህበር ጋር በመተባበር የስልጠና እና የምክር አገልግሎት የሚሰጥበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ✓ የኤክስፖርት አፈፃፀምና ለገበያው የሚቀርቡ የሆርቲካልቸር ምርቶች ከደንበኛው ፍላጎት አንፃር እንዲሁም ከየሀገሩ መመሪያ በተጣጣመ መልኩ በጥራት፣ በአይነትና በመጠን በወቅቱ ተሟልቶ እንዲቀርብ ኤጀንሲው የገዢዎችን ሀገራት የጥራት ፍላጎት ደረጃዎችን ለይቶ መረጃዎችን በማጠናቀር ለአምራች ላኪዎች አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ለሆርቲካልቸር ኤክስፖርት የሚሆኑ አገራዊ የፓኬጂንግ ስታንዳርድ (specification and standard) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በብዛት የሚመረትባቸው አካባቢዎች (አርቦ ምንጭ፣ ራያቆቦ፣ ምሰራቅ ሀረርጌና ድሬደዋ) የተሟላ የምርት ማደራጃና ማከማቻ መጋዘን ሊኖር ይገባል፡፡
- ✓ ኤጀንሲው የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብና ለባለሀብቶች ሊያሰራጭ እና ዋና ዋና ገበያዎችን በማየት ባለሀብቶችን ለመደገፍ የሚያስችል የገበያ መረጃ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ኤጀንሲው በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዳ የመረጃ መረብ (Web Site) ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ዘርፉን የሚመለከቱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በየጊዜው ሲወጡም ሆነ ሲቀየሩ ኤጀንሲው በወቅቱ ለባለሀብቶች እንዲያውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ዘርፉ የሚጠይቀውን አገልግሎት ከማቀላጠፍና ከማሳደግ ረገድ ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ቅንጀታዊ አሰራር ሊኖረው ይገባል፡፡
- ✓ ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች፣ በምርምር ማዕከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ኤጀንሲው ዓመታዊ ዕቅድ ሲያዘጋጅ የስትራቴጂክ ዕቅዱን መሰረት ሊያደርግና በዕቅድ ዝግጅት ወቅት በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችንና የሚመለከታቸው አካላትን አሳታፊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

135. በአጠቃላይ በሀገሪቱ የየአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የወጪ ንግድ አፈፃፀም በአግባቡ እንዲካሄድ ለማድረግ ብሄራዊ ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና በዘርፉ የወጡ አለም አቀፍ ስምምነቶችን ጥናትን መሰረት በማድረግ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግና አፈፃፀማቸውን ለመከታተል የተጠናከረ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ለመዘርጋት እና ተግባራዊ ለማድረግ ኤጀንሲው፣ የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም በአትክልትና ፍራፍሬ ዙሪያ የተሰማሩ ባለሀብቶች ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ይህንንም ለማሳካት በፌዴራል እና በክልል የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ በዚህ ሪፖርት የተገለጹት ግኝቶች፣መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሃሳቦች በቀጥታ ኤጀንሲውን ሙሉ ለሙሉ የማይመለከቱ ቢኖሩ፣ ኤጀንሲው በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሃሳቦች ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ፣ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የፌዴራል እና የክልል እና የዞን መ/ቤቶች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም ባለሀብቶች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ:- የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የውጪ ንግድ አፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን መገምገም፤

## ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት:- የኢትዮጵያ ሖርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ

| የኦዲት ጭብጥ | የኦዲት ንዑስ ጭብጥ (Sub-Issues) | የመገምገሚያ መስፈርት (Evaluative criteria) |
|---|---|---|
| 1. ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በተመለከተ የኢንቨስትመንት ድጋፍ አሰጣጥ፣ የማበረታቻ ስርዓትና በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የተዘረጋው አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ | 1.1 የኢንቨስትመንት ድጋፍ አገልግሎት ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል የአሰራር ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤ | 1.1.1 የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንትን ለማቆየት፣ ለመሳብና ለማበረታታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ:- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 1.1.2 የክልል ልማቶችን ተጨባጭ ሁኔታ በገመገመ መልኩ የኤክስፖርት ልማቱን በሁሉም አካባቢ ለመሳብ የሚያስችል የኢንቨስትመንት የማትጊያ ስርዓት ተጠንቶ ክልሎችን ባሳተፈ መልኩ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ:- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 1.1.3 ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር በመሆን ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉ ማሳዎችን በዝርዝር ሊያጠና እና ለኢንቨስትመንት አመቺ መሆናቸውን በማረጋገጥ የማስተዋወቅ ስራ የሚሰራበት አሰራር ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ:- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 23) |
| | | 1.1.4 በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዱ የመረጃ ቋት በመፍጠር የዚሁ መረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ:- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 2፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 1.1.5 ኤጀንሲው በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ለአዋጭነት ጥናት የሚያግዙ መረጃዎች ሊያሰባስብ፣ ሊያደራጅ እና ሊያቀርብ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ:- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 2፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 11) |
| | | 1.1.6 በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ የሚገቡ ባለሀብቶች ደረጃውን የጠበቀ፣ አዋጪነቱ አስተማማኝ የሆነና ጥናቱ ሊተገበር የሚችል የአዋጪነት ጥናት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ:- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 2፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 1.1.7 ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬትና የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ የሚመቻችበት እና አፈፃፀሙን በቅርበት ክትትል የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደረግ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 2፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 11) |
| | | 1.1.8 ኤጀንሲው በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች በወቅቱ የመሰረተ ልማት አገልግሎት(ውኃ፣ መብራት፣ ስልክ፣ መንገድ፣ ወዘተ) እንዲያገኙና ለግንባታ ከውጪ ሀገር የሚገዙ ግብዓቶች እንዲገቡ እንዲሁም ከሀገር ውስጥ የሚገዙት ግብዓቶች በወቅቱ እንዲቀርቡ ድጋፍ የሚያደረግበት ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 3፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 11) |
| | | 1.1.9 በኢንቨስትመንት ረገድ የሚወጡ አዳዲስ ወቅታዊ መመሪያዎችን ባለሀብቶች በወቅቱ እንዲያውቁ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 3፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ |
| | | 1.1.10 ኤጀንሲው አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስ፣ ወዘተ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 3፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 1.1.11 የባለሀብቶችን የካፒታል አቅም ለማጎልበትና ወደ ልማት በአፋጣኝ እንዲገቡ ለማድረግ ባለሀብቶች ከፋይናንስ ተቋማት የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍና ለሚያጋጥማቸው ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 3፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 1.1.12 ከፌዴራልና ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር አትክልትና ፍራፍሬ ልማቶችን በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 3፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 1.1.13 ኤጀንሲው ለክላስተር የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉ ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በአግባቡና በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን የሚረጋገጥበት እና የተሰጡ ድጋፎች ለታቀደላቸው ዓላማ መዋላቸውን ክትትል የሚያደርግበት አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 11) |
| | | 1.1.14 ኤጀንሲው መሬት ወስዶው ወደ ልማት ያልገቡ ባለሀብቶች በአግባቡ ተለይተው በአፋጣኝ ወደ ልማት እንዲገቡ ካልሆነም እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር ዘርግቶ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 3፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 1.1.15 በኤጀንሲውና በአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች መካከል የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር ለመፍጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 3፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 1.1.16 የባለሀብቱ የመሬትና የመሰረተ ልማት ጥያቄ ለመመለስ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመደበኛነት ለመገናኘት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.2 በመንግስት የወጡ ልዩ ልዩ የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች በአግባቡ ስራ ላይ የሚውልበትና ኢንቨስትመንቱን ከመደገፍ አንፃር የሚከሰቱ ችግሮች በወቅቱ በመለየት አፋጣኝ መፍትሔ የሚሰጥበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣ | 1.2.1 የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ግብዓቶች በወቅቱ እንዲቀርቡ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 1.2.2 ሞዴል የሆኑ የአትክልትና ፍራፍሬ ኩባንያዎች በመምረጥ ልዩ ልዩ ማበረታቻዎች እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 1.2.3 ኤጀንሲው በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ችግሮች በመዳሰስ አፋጣኝ ምላሽ በወቅቱ እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| 2. ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምርት እና ምርታማነትን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ስርዓት ዘርግቶ በአገር ውስጥ እና በአለም አቀፍ ገበያ ጥራቱን የጠበቀ ተወዳዳሪ ምርት ለማምረት እንዲችሉ የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣ | | 2.1 ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን ውጤታማ የሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎችን ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ከአገር ውስጥና ከውጪ አገር ሊሰበሰብ እና የተሰበሰቡትን ቴክኖሎጂዎች በመገምገም በስልጠና እና ሰርቶ ማሳያ ላይ ለተጠቃሚዎች ሊያስተዋወቅ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 2.2 ኤጀንሲው በግብዓት አቅራቢነት የተሰማሩ ኩባንያዎች ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በዓይነትና በመጠን እንዲቀርቡ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግና እጥረት በሚፈጠር ወቅት በማስተባበር ችግሩን የሚፈታበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 2.3 ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች አፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ የሚደረግበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | (ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | 2.4 የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች ሊሰበሰቡ፣ ሊደራጁና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡<br><br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | 2.5 ለባለሀብቶችና ገበሬዎች ልማት ላይ የመስኖ አጠቃቀም፣ የአግሮኖሚ እንክብካቤ፣ ዝርያ አመራረጥ፣ ምርት አጠባበቅና ሌሎች የአትክልትና ፍራፍሬ ቴክኖሎጂ ፓኬጅ ያካተተ የሙያ ማሻሻያ አውደ ጥናትና ስልጠና በተከታታይ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡<br><br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | 2.6 ኤጀንሲው በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች አለም አቀፍ መስፈርቶችን(የዩሮ ጋፕ(የአውሮፓ ህብረት የግብርና ሰብሎች አመራረትና እንክብካቤ የጥራት መስፈርት)) የአሰራር ስርዓትን እንዲያውቁት ሊደረግ እና መስፈርቶቹን ተከትለው ስለማከናወናቸው ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡<br><br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | 2.7 ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትና ምርት አያያዝ የአፈፃፀም ማንዋሎች ሊያዘጋጅ ፣ ስልጠና ሊሰጥና ወደ አርሶ አደሩ መውረዱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡<br><br>(ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 11) |
| | 2.8 ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ በኮንትራት ልማት የሚሳተፉ አርሶ አደሮች(አውትግሮወሮች) በመመልመል እንዲደራጁ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br><br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 5፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 11) |
| | 2.9 ኤጀንሲው ለኮንትራት አርሶ አደሮችና ለክልል ባለሙያዎች የስልጠናና የቴክኒክ ድጋፍ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡<br><br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 5፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 12) |
| | 2.10 ኤጀንሲው አውትግሮወሮች ከምርት ላኪ ድርጅቶችና ዩኒየኖች ጋር በጋራ የሚሰሩበት የአሰራር ስርአት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡<br><br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 5፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 11) |

| | | |
|---|---|---|
| 3. ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ጥራቱን የጠበቀ እና ተወዳዳሪ ምርት ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል ማድረጋቸውን እንዲሁም ከአልሚ ባለሀብቶች፣ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | 3.1 በዘርፉ የተሰማሩ ባለሃብቶች ጥራቱን የጠበቀ እና ተወዳዳሪ ምርቶችን ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ የገበያ ጥናት በማካሄድ ትስስር መፍጠሩን፣የውጭ ንግድ የምርቶች ሽያጭ የመንግስት ፖሊስን ተከትሎ መፈፀሙን መገምገም፣ | 3.1.1 ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላኪ ድርጅቶችና ዩኒየኖች የውጪ ንግድ የምርት ሽያጭ ሲያከናውኑ የመንግስት ፖሊሲ፣ መመሪያና ደንብን ተከትለው መፈፀማቸውን ሊከታተል፣ ሊቆጣጠር እና ሊያረጋገጥ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 24 እና 26) |
| | | 3.1.2 ኤጀንሲው በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የሚከናወኑ የሆርቲካልቸር ልማት ስልጠናዎች፣ አውደጥናቶች፣ ኤግዝብሽኖች እና የንግድ ትርኢቶች ዝርዝር በመያዝ የአትክልትና ፍራፍሬ ሰብል አምራቾችና ነጋዴዎች እንዲሳተፉ ድጋፍ የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 11፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 27) |
| | | 3.1.3 ኤጀንሲው የምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎች በተፈጸመው ውል መሰረት የጥራት ደረጃቸውንና አይነታቸውን ጠብቀው በወቅቱ መዘጋጀታቸውን የሚከታተልበት ፣ የሚቆጣጠርበት እና ድጋፍ የሚያደረግበት ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 24 እና 26) |
| | | 3.1.4 ኤጀንሲው ለውጪ ንግድ የሚቀርቡ ምርቶች በብዛት ፣ በጥራት እና በአይነት ከተያዘው እቅድና ከተፈፀመው ውል ጋር የተጣጣሙና ትክክለኛ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርአት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 24 እና 26) |
| | | 3.1.5 ኤጀንሲው አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን ለማስፋፋት መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርአት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 27) |
| | 3.2 በዘርፉ የተሰማሩ ባለሃብቶች ጥራቱን የጠበቀ ምርት ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ባለሃብቶች ለማቅረብ ኤጀንሲው ከአልሚ ባለሀብቶች፣ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር | 3.2.1 ኤጀንሲው የገበያ መረጃዎችን ሊያሰባስብ ፣ ሊያሰራጭና ተጠቃሚዎች ወደ ገበያው መግባታቸውን ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 11፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 27) |
| | | 3.2.2 ኤጀንሲው የገዢዎችን ሀገራት የጥራት ፍላጎት ደረጃዎችን ለይቶ መረጃዎች በማጠናቀር ለላኪዎች ሊያሰራጭና አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 24 እና 26) |

| | | |
|---|---|---|
| | በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥመገምገም፤ | 3.2.3 ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዣ፣ የትራንስፖርትና ሌሎችም የሎጂስቲክስ ፍላጎቶች ከሌሎች ሀገሮች ልምድ በመነሳት በማጥናት ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ <br><br> (ምንጭ፡-የኢ.ትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 9፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 28) |
| | | 3.2.4 ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት ምርቶች በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪነታቸውን ለማረጋገጥ ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ በመነሳት የተሻለ አመራረት፣ ጥራትና የምግብ ደህንነት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲኖር ከሆርቲካልቸር ማህበር እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የስልጠና እና የምክር አገልግሎት የሚሰጥበት የአሰራር ስርአት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ <br><br> (ምንጭ፡-የኢ.ትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 7) |
| | | 3.2.5 ኤጀንሲው የሆርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለሙያዎች የሚሳተፉበት ቋሚ እና መደበኛ መድረክ በማመቻቸት በጋራ ለልማቱ የሚያግዙ እርምጃዎች የሚወሰድበት የአሰራር ስርአት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ <br><br> (ምንጭ፡- የኢ.ትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 11) |
| | | 3.2.6 በምርምር ማዕከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላቦራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡ <br><br> (ምንጭ፡- የኢ.ትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 12) |
| | | 3.2.7 ኤጀንሲው የስትራቴጂክ ዕቅዱን መሰረት በማድረግ ዓመታዊ ዕቅድ ሊያቅድና አፈፃፀሙ ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች መንስኤዎቻቸውን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ <br><br> (ምንጭ፡- የኢ.ትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር 152/2008 አን.5 ንኡ/አን 5፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ) |
| | | 3.2.8 ኤጀንሲው በዕቅድ ዝግጅት ወቅት ነባራዊ ሁኔታን በትክክል ባገናዘበ መልኩ ሊያቅድ፣ የዕቅድ ዝግጅቱ ዋና ፈፃሚንና ባለሀብቱን አሳታፊ ሊያደርግ እና መድረክ በመፍጠር ሁሉንም ሰራተኞችና ባለሀብቶች ዕቅድ ላይ በቂ ኦረንቴሽን ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | | 3.2.9 ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው የፌዴራል መ/ቤቶች፣ ክልሎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት አካባቢ አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን ክትትል የሚያደርግበት የአሰራር ስርአት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ <br><br> (ምንጭ፡- የኢ.ትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የደሞዝ ስኬልና ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ገፅ 23) |

## አባሪ 2 ፡የኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት የስራ ፍሰት

የኢንቨስትመንት ድጋፍ አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን በየወቅቱ ማሻሻያዎችን እያደረገ ወጥ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

በመንግስት የወጡ ልዩ ልዩ ማበረታቻዎች በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል

ኢንቨስትመንት ከመደገፍ አንፃር የተከሰቱትን ግድፈቶች ያርማል በቀጣይነት ቀልጣፋና ውጤታማ ስራ ይሰራል

ኢንቨስትመንትን ለማቆየት፣ ለመሳብና ለማበረታታት የሚያስችል ስልት ነድፎ ይተገብራል

የኢንቨስትመንት ተግባራትን ከጫፍ ጫፍ በማከናወን በቅንጅት ላይ የተመሰረተ ስራ ይሰራል

ከኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ ይተገብራል

ለባለሀብቶች በአነስተኛ ጊዜ ውስጥ የውኃ፣ የመብራት፣ የስልክ፣ የመንገድ፣ ወዘተ የመሰረተ ልማት አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ያደርጋል

ለደንበኞች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የኢንሹራንስ፣ ወዘተ አገልግሎቶችን ይሰጣል

ከክልል ጋር የቅርብ የስራ ግንኙነት ይፈጥራል፤ የመሬት አቅርቦትና ከመሬት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በወቅቱ ይሰጣል

በሆርቲካልቸር ኢንዱስትሪ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ችግሮች በመዳሰስ አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙ ያደርጋል

ኢንቨስትመንቱ ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዱ የመረጃ ቋት በመፍጠር የዚሁ መረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል

የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ግብዓቶች በወቅቱ እንዲቀርቡ ያደርጋል

በኢንቨስትመንት ረገድ የሚወጡ አዳዲስ ወቅታዊ መመሪያዎችን ባለሀብቶች በወቅቱ እንዲያውቁ ያደርጋል

ለሆርቲካልቸር ባለሀብቶች የተሰጡ ድጋፎች ለታቀደላቸው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል

በኤጀንሲውና በሆርቲካልቸር ልማቶች መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ለመፍተር ሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል ይተገብራል

ሞዴል የሆርቲካልቸር ኩባንያዎች በመምረጥ ልዩልዩ ማበረታቻዎች እንዲያገኙ ያደርጋል

በሆርቲካልቸር ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በወቅቱ የግንባታ ማቴሪሎች እንዲያገኙ ያደርጋል

ከፌዴራልና ከክልል የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የሆርቲካልቸር ልማቶች በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ ያደርጋል

## አባሪ 3፡ የልማትና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት የስራ ፍሰት

የአትክልት፣ ፍራፍሬና ኸርብል የግል አልሚዎች አፈፃፀም ክትትል ያደርጋል፣ችግሮችን ይለያል ፣ድጋፍ ይሰጣል

↓

በሆርቲካልቸር ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሙያዎች ለአዋጭነት ጥናት የሚያግዙ መረጃዎች ያቀርባል ፣ክልሎች ጋር በመተባበር መሬትና የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ ያመቻቻል አፈፃፀሙን በቅርብ ይከታተላል

↓

ከሆርቲካልቸር ማህበር ጋር በመተባበር ልማቱ የዩሮጋፕን፣ ሌሎች የእርሻ ማህበር ሰራ አመራር ደንቦችን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል ሰልጠናና ምክር አገልግሎትም ይሰጣል

↓

ለክላስተር የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉ ፣እንዲሁም ለተመሳሳይ የግብርና ኢንቨስትመንት ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በአግባቡና በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ድጋፍ ይሰጣል ከክልሎች ጋር በመተባበር የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል

↓

ባለሀብቱ በወቅቱ የመሰረተ ልማት አገልግሎት እንዲያገኝና ለግንባታ ከውጭ ሀገር የሚገዙ ግብአቶች እንዲገቡ እንዲሁም ከሀገር ውሰጥ የሚገዙ ግብአቶች በወቅቱ በወቅቱ እንዲያቀርቡ ድጋፍ ያደረጋል

↓

የሆርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለሙያዎች የሚሳተፉበት ቋሚ መድረክ በማመቻቸት በጋራ ለልማቱ የሚያጋዙ እርምጃዎችን ይወሰዳል

↓

በውጭ ሀገር የሚካሄዱትን የሆርቲካልቸር ልማት ሰልጠና ፣አውደ ጥናትና ኤግዚብሽን ያሰተባብራል አፈፃፀማቻን ይከታተላል

↓

የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶችን ያሳሰባል ፣አዳዲስ የሰብል አመራረት አያያዝ ኤክሰቴንሽን ፓኬጆችን ያዘጋጃል የተሰሩትን ያሻሽላል ያሰራጫል

↓

ምርመራን ተቋማያዊ እንዲለቀቁ በሚቀርቡ የአትክልትና ፍራፍሬ ዝሪያዎች ግምገማ ላይ አብሮ ይሰራል ከክልሎች ጋር በመተባበር የሚለቀቁ ዝሪያዎች ፈጥነው ወደ ልማት የሚሸጋገሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል

↓

በምርምር ማእከላት በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላቦራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ድጋፍ ይሰጣል፣ በዘር አቅርቦት ረገድ ልማቱን ማገዛቸውን ያረጋገጣል

↓

የካንትራት የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ደጋፊ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ይከታተላል ድጋፍ ይሰጣል ጠቃሚ ልምዶችን በመውሰዱ ክልሎችን ጋር በመተባበር እንዲስፋፉ ያደርጋል

## አባሪ 4፡ የገበያ ማስፋፊያ ጥናትና ጥራት ክትትል ዳይሬክቶሬት የስራ ፍሰት

የሆርቲካልቸር ምርት ላኪ ድርጅቶችና ዩኒዮኖች የውጭ ንግድ የምርት ሽያጭ የመንግሰት ፓሊሲ፣መመሪያና ደንብ ተከትሎ መፈጽሙን ያረጋግጣል ፣ይቆጣጠራል፣እንደአሰፋላጊነቱ የማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል ሲፈጽም ተግባራዊነቱን ይከታተላል

↓

የሆርቲካልቸር መዳረሻ ገበያዎችን ያጠናል ፣መረጃዎችን ያሰባሰባል የገኘውን ሀገር የጥራት ፍላጎትና ሌሎች ደረጃን የሚመለከት መመሪያ ያዘጋጃል ፣ለላኪዎች ያሰራጫል

↓

ከሆርቲካልቸር ማህበር ጋር በመተባበር ለውጭ ንግድ የሚቀርበው ምርት ከተያዘው እቅድና ከተፈፀመው ውል ጋር ጥራቱንና አይነቱን ትክክለኛ መሆኑን ያረጋግጣል

↓

ከሆርቲካልቸር ማህበር ጋር በመተባበር የምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎችን በተደረገው ውል መሰረት የጥራት ደረጃቸውንና አይነታቸውን ጠብቀው በጊዜው መዘጋጀታቸውን ይከታተላል ፣ድጋፍ ይሰጣል

↓

ከሆርቲካልቸር ማህበር ጋር በመተባበር ምርቱ የሚጓጓዝበት የየብሰ ፣የአየርም ሆነ የባህር ትራንሰፓርት ዝግጅት በቅድሚያ ፕሮግራም የወጣለትና የተጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል ፣ድጋፍ ይሰጣል

↓

የሆርቲካልቸር አምራችና ላኪዎች የግል ድርጀቶችና የአርሶ አደሮች ዩኒዬኖች ምርታቸውን ለማሰተዋወቅና ደንበኞችን ለማፍራት እንዲችሉ በሀገር ውሰጥና በውጪ ንግድ ትርኢቶች ዝገጅት ያመቻቻል

↓

ጥራቱን የጠበቀ የንግድ መሰረተ ልማት ግንባታና ድጋፍ ሰጪ ኢንዷሰትሪዎችና አገልግሎቶች እንዲሰፋፉ ጥናት ያቀርባል ድጋፍ ይሰጣል፣አፈፃፀሙን ይከታተላል

↓

የባለሙያዎች የገበያ ማሰፋፊያ መረጃ ማእከልና የገበያ ጥናትና ክትትል ሰራ ጥራቱን የጠበቀ ቀልፋና አሰተማማኝ እንዲሆን ያደረጋል

↓

ከኤጀንሲው ጋር ተዛማጅና ተደጋጋፊ የሆኑ ተግባራትን የሚያከናውኑ ተቋማዊ /ድርጀቶች ጋር በመተባበር ይሰራል፣ይደግፋል ፣ያበረታታል ጠቃሚ ተመክሮችን ያሰተላልፋል የግብረ መልሰ ሰራዎችን ይከታተላል

**አባሪ 5፡ በናሙና የተመረጡ ክልሎችና ካምፓኒዎች በአካል በመሄድ መረጃ የተሰበሰበባቸው**

| ተ.ቁ | የክልሎች ዝርዝር | ከተማ/ወረዳ | የካምፓኒዎች ዝርዝር |
|---|---|---|---|
| 1. | ደቡብ | ሀዋሳ | የክልሉን የኢንቨስትመንት ቢሮ |
| | | | አልሜታ ኢምፔክስ |
| | | አርባ ምንጭ | ሙላት ኃይሌ፣ አሞቲክ፣ አምኒባራ፣ |
| | | | አውትግሮዎር ዩኒየን |
| | | | የጋሞ ጎፋ የኢንቨስትመንት ቢሮ |
| 2. | ኦሮሚያ | አዲስ አበባ | የክልሉን የኢንቨስትመንት ቢሮ |
| | | ሆለታ | ድሬ እና ጂቱ ኩባንያዎች |
| | | ቆቃ | ኢትዮ ቬዥ ፍሩት፣ |
| | | አዋሽ | የላይኛው አዋሽ, ዘጊቪንግ ትሪ ነርሰሪ |
| | | ዝዋይ | አውትግሮዎር ዩንየን |
| | | ሰበታ | ኦሜጋ ፋርም |

**በናሙና ተመርጠው የተከለሱ የካምፓኒ ፋይሎች(አልሜታ ኢምፔክስ፣ ዘጊቪንግ ትሪ ነርሰሪ፣ ድሬ፣ ጂቱ፣ ኢትዮ ቬጅ ፍሩት፣ የላይኛው አዋሽ፣ ኦሜጋ ፋርም፣ ግርን ማርክ ዩኒ ፍሩት፣ ጆይ ቴክ፣ ሉና ፍሩት፣ በጅድ ባዲ፣ ፓም ጎልድ፣ ጎልደን ቢን፣ ኢትዮ ፍሎራ እና የላይኛው አዋሽ)**